ፋዌ
ኢትዮጵያ
FAWE
Ethiopia

# ትማር
# TIMMAR

## ፋዌ ኢትዮጵያ ብሄራዊ ቻፕተር ዓመታዊ መጽሄት
## FAWE-Ethiopia National Chapter Annual Magazine




ቅፅ 20/Volume 20
ታህሳስ 2014/DECEMBER 2021

## Vision

FAWE-Ethiopia's Vision is to see a country in which there is no gender disparity in the education of the country.

## Mission

In line with the vision, FAWE Ethiopia's mission is also derived from the Regional Secretariat's. In partnership with strategic partners, national governments, educators, researchers, influencers and local communities, FAWE Ethiopia Chapter will foster innovations, promote positive policies/practice and provide opportunities for girls and young women, especially those in extreme adversity, to develop skills and competencies that will allow them to be productive members of their societies.

## General goal

The general goal is to empower girls and women in Ethiopia with all-rounded employable skills, values and competencies they need to achieve their full potential.

## Strategic goal

SO1: Girls and young women including disabled, displaced, Women living with HIV/AIDS, and those marginalized across the regions and city administrations of Ethiopia have access to quality education and training opportunities to develop relevant skills for the world of work.
SO2: Education systems in Ethiopia integrate gender-responsive approaches and policies to nurture skills and competencies for girls and women to contribute to their societies.
SO3: FAWE Ethiopia Chapter has the institutional capacity developed (networking, leadership, technical & financial) to deliver its mandate to the best level
SO4: FAWE Ethiopia Chapter has in place research and knowledge management systems to inform policies, new approaches and set pace for girls' agenda in Ethiopia's development platforms.

## Values

FAWE Ethiopia Chapter values professionalism, accountability, and integrity. We are passionate about results, and are dedicated in everything we do.

## Governance

- General assembly
- Board

The board has 7 members 100% female.

## Management committee

The management committee has 4 members with 50% female

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| የፋዌ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ዳይሬክተር መልዕክት | 1 |
| የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዓመታዊ የሥራ ክንውን | 2 |
| ዓረብ ቤት የሚባለው የመንደር ገበያ መለወጥ | 9 |
| የፋዌ ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተሮች የ2013 ዓ.ም. የሥራ እንቅስቃሴ | 10 |
| የፋዌ ኢትዮጵያ የቀድሞ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚዎች ዓመታዊ ጉባኤ እና የ2013 ዓ.ም. ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች የምረቃ ሥነስርኣት | 13 |
| የፋዌ ኢትዮጵያ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪ ምስክርነት | 14 |
| ከአርኣያዎች አንደበት | 16 |
| የትማር እንግዳ | 17 |
| የፋዌ ኢትዮጵያ ስኬት አንዱ መገለጫ | 21 |
| የሴቶችን መማር አስፈላጊ የሚያደርጉ 10ሩ ምክንያቶች | 23 |


## CONTENTS


| | |
|---|---|
| Message from FAWE Ethiopia Executive Director | 25 |
| Overview of FAWE-Ethiopia's Annual Accomplishments | 26 |
| Successful FAWE Ethiopia scholarship beneficiary student | 32 |
| Muluemebet Emiru፡ Africa's First Female Pilot in 1936 | 33 |
| Most Significant Change Story (MSCS): Changes in Social Norms | 33 |
| Timmar Guest | 34 |
| Top 10 facts about girls' education in developing countries | 37 |
| FAWE Ethiopia Sub-chapters annual accomplishments | 37 |
| 4th National Alumni Conference and 4th Cohort scholars graduation ceremony | 39 |
| Number of countries with women in highest position | 41 |
| How the "Arab Bet" Shops Changed Hands | 41 |


### FAWE Ethiopia Collaborators:

Ministry of Education
Regional Finance and Economic Development Bureaus
Regional State Educational Bureaus
Regional States Women and Social Affair Bureaus
FAWE Sub-Chapters
MasterCard Foundation/MCF
Civil Society Support Programme 2/CSSP2
Malala Foundation
Plan International Ethiopia
Dutch Ministry of Foreign Affairs
VSO
International Institute for Education/IIE
Basic Education-Network Ethiopia
Network of Ethiopia Women's Associations/NEWA
DSW-Ethiopia


አርታኢያን/Editors
ሮማን ደገፋ
Roman Degefa
ጌትነት ማሞ
Getenet Mammo
ብሌን ብርሃኔ
Blen Brhane
Publisher:
FAWE Ethiopia Chapter
Phone Numbers: Office- 011-6-676645
011-6-676679
Fax: 011-6-676657
E-mail: fawe@faweethiopia.org
P.O.Box: 20882,Code 1000
Designed and Printed by:
MM Printing
E-mail: mmprinting22@gmail.com
Mobile Numbers: +251011 868 8685
+251911 24 7878



# የፋዌ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ዳይሬክተር መልዕክት

እንደሚታወቀው፣ በሃገራችን ትምህርትን የተመለከቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀርፀው ሲተገበሩ ቆይተዋል። ሆኖም፣ ሃገራችን ካለችበት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የተነሳ፣ እነዚህን የትምህርት ፖሊሲ አቅጣጫዎች ሴኬታማ ከማድረጉ ጎን ለጎን ተግዳሮቶች ማጋጠማቸው አልቀረም፥ ፥ ዛሬም በሚፈለገው እና በታቀደው መሰረት ትምህርትን በጥራትና በፍትሃዊነት በማዳረስ ረገድ ችግሮች መስተዋላቸው አልቀረም። በመሆኑም፣ እነዚህን ችግሮች በሚገባ ቀርፎ የሃገራችንን እድገትና ልማት ለማፋጠን ከመንግስት ባሻገር ያሉ አካላት እንቅስቃሴ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። በዚህም መሰረት፣ ከዚህ አውነታ በመነሳት ባለፉት ዓመታት ትምህርቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችሉ ተግባራት በህብረተሰቡና በተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ተከናውነዋል።

በሃገራችን፣ የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ቁጥር የሚበልጥ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። እነዚሁ መረጃዎች፣ ዘርፈ ብዙ የሆኑት ችግሮቻችን፣ በተለይም ማህበራዊና ቤተሰባዊ ጉዳዮች፣ በአብዛኛው የወደቁት በሴቶች ጫንቃ ላይ መሆናቸውንም በተጨማሪ ያመለክታሉ። ይህ ደግሞ፣ ሴቶች ትምህርትን በመሳሰሉና ለሃገር ልማትና እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ባላቸው ጉዳዮች ላይ በሚኖራቸው የነቃ ተሳትፎ ላይ የሚኖረው ተፅእኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ስለሆነም፣ ሴቶች ሃገራዊ በሆኑ የልማትና የእድገት እንቅስቃሴዎች ላይ ከአስካሁኑ የበለጠ ጉልህ አስተዋፅኦና ድርሻ ይኖራቸው ዘንድ፣ ከሴቶች የትምህርት ፍትሃዊነት፣ ተጠቃሚነትና ተደራሽነት ጋር የተገናዘቡ እንቅስቃሴዎች ከአስካሁኑ በተለየ ሁኔታ እንዲተገበሩ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ርብርባቸውን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል።

በተለይም፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሴቶች የትምህርት ተሳትፎ መሻሻል ላይ ያደረጉት እንቅስቃሴ፣ በትምህርቱ ዘርፍ ለሚስተዋሉ ችግሮቻቸው መቀረፍ የነበረው አስተዋፅኦና ድርሻ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በሴቶች የትምህርት ተሳትፎ እድገትና ውጤታማነት ላይ አስተዋፅኦ ከነበራቸው ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል አንዱ ፋዌ ኢትዮጵያ ነው። ፋዌ ኢትዮጵያ፣ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በመሆን ከተቋቋመበት ከ1986 ዓ.ም. አንስቶ፣ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖዎች ተጋላጭ የሆኑ ሴት ተማሪዎችን ያማከሉ ፕሮግራሞችን በመቀየስ በትምህርቱ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል፤ በማድረግም ላይ ይገኛል፥ ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከምስረታው ጊዜ አንስቶ ባከናወናቸው ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች፣ በተለያዩ ችግሮች የተነሳ ከትምህርት ገበታቸው ሊሰናከሉ የሚችሉ በርካታ ሴት ተማሪዎችን መታደግ ችሏል፥ ፥ለዚህም በተለያዩ ፕሮግራሞቹ ተጠቃሚ ሆነው ትምህርታቸውን እስከከፍተኛው የትምህርት እርከን ድረስ በመጓዝ በውጤታማነት ማጠናቀቅ የቻሉና ለሃገር ጠቃሚ በሆኑ ሥራዎች ላይ በመሰማራት ሃገራቸውን በማገልገል ላይ የሚገኙ ሴት አህቶቻችን ምስክር ናቸው።

በመጨረሻም፣ ፋዌ ኢትዮጵያ፣ እነዚህን ለሃገር አለኝታ የሆኑ በርካታ ዜጎችን ለቁም ነገር ለማብቃት ባከናወናቸው ተግባራት ሁሉ፣ ለፕሮግራሞቹ ስኬታማነት የበኩላቸውን ሚና ለተጫወቱና በተለያዩ ድጋፎቻቸውም ከጎኑ ለነበሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ ያለውን አክብሮትና ምስጋና በድርጅቱ ስም በዚህ አጋጣሚ አገልግለሁ። በቀጣይም፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር የፈጠረውን መርህ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት የሚያጠናክሩ እንቅስቃሴዎችን በትጋት እንደሚፈፅም፣ በተቋቋመበት ዓላማ መሰረትም በስኬታማ ጉዞው እንደሚቀጥል ያለኝን ተስፋና እምነት አስታውቃለሁ።

# የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዓመታዊ የሥራ ክንውን

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በ1993 (እ.ኤ.አ.) በ34 የአፍሪካ ሃገራት የተቋቋመው የፋዌ አህጉራዊ ቻፕተር መሥራች ሃገር በቀል ድርጅት ነው። እ.ኤ.አ. በ2021 የማህበረሰብ በጎ አድራጎት ድርጅት በመሆን በዳግም ምዝገባ የመንግስትን እውቅና ያገኘው ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከምሥረታው ጊዜ አንስቶ በተቋቋመበት ዓላማ መሰረት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፤ አያከናወነም ይገኛል። በተለይም፣ በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተግዳሮቶች የተነሣ በትምህርታቸው የመዝለቅ አደጋ የተጋረጠባቸውን ሴት ተማሪዎችን በበርካታ ፕሮግራሞቹ አማካይነት ታድጓል። ከምስረታው ጊዜ አንስቶ ባከናወናቸው በነዚህ ፕሮግራሞቹ በኩል በሺዎች የሚቆጠሩ ሴት ተማሪዎች ተጠቃሚ መሆን በመቻላቸው፣ አብዛኞቹ ትምህርታቸውን በስኬት በማጠናቀቅ ሃገራቸውን በተለያዩ የሥራ መስኮች በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በአሁኑ ወቅትም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት በመፈፀም ላይ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል፣ “ MasterCard Foundation Scholars Program, Break Free, Malala Foundation Global COVID-19 Initiative, Make Way and CSSP2 granted Bearers of Life “ የተሰኙት ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ፕሮጀክቶች፣ በሶስት ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ማለትም፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በሲዳማ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ወረዳዎችና ክፍለ ከተሞች በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። በዓመቱም የተለያዩ አዎንታዊ ውጤቶች ተመዝግበዋል። እርግጥ፣ በዓመቱ በተመዘገበው ውጤት ላይ ተፅእኖ ያደረጉ ጉዳዮች መኖራቸው አልቀረም። በዚህም መሰረት፣ ዓመቱ ኮቪድ-19 በመማር መስተማሩ ሂደት ላይ አሳድሮት የነበረው ተፅእኖ እና በሃገራችን በከፍተኛ ደረጃ የተስተዋለው የዋጋ ግሽበት በዚህ ረገድ በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚህን የተለያዩ ፕሮግራሞች መሰረት በማድረግ፣ በተጠናቀቀው የፈረንጆቹ 2021 ዓ.ም. ላይ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። የእነዚህን ተግባራት የአፈፃፀም ሁኔታ፣ ከፍ ብለን የዘረዘርናቸውን ፕሮጀክቶች መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው እናቀርባለን::

## “ማስተርካርድ ፋውንዴሽን /MasterCard Foundation” ፕሮጀክት

የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም፣ በትምህርት ውጤታቸው የተሻሉ ሆነው ነገር ግን፣ በኢኮኖሚ ጫና የተነሣ ጥራት እና ተገቢነት ያለው የ2ኛ ደረጃ እና የዩንቨርስቲ ትምህርት ተደራሽ ያልሆነላቸውን ወጣት ተማሪዎችን የመታደግ ዓላማ አለው። እ.ኤ.አ በ2013 ዓ.ም. የተጀመረውና የ10 ዓመት የቆይታ ጊዜ ያለው ይህ ፕሮግራም፣ በተለየ መልኩ ለአፍሪካ ወጣት ተማሪዎች የበለጠ ትኩረት በመስጠት፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ በሁለት የአፍሪካ ሃገራት (ሩዋንዳ እና ኢትዮጵያ) በመተግበር ላይ ይገኛል፡ ፡ በዚህ የፕሮግራሙ ዓለማ መሰረት፣ በፕሮግራሙ የሚታቀፉ ተማሪዎች በትምህርት ሂደታቸው ውስጥ የተለያዩ ትምህርታቸውን ሊያግዙ የሚችሉ ድጋፎች ይደረግላቸዋል። ከድጋፎቹ ውስጥም የፋይናንስ፣ የአካዳሚና ማህበራዊ ጉዳዮችን ያካተቱ በዋናነት ይጠቀሳሉ። ፕሮግራሙ እየተተገበረ ያለው፣ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የትምህርት ተቋማትና ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች የጋራ ትብብር ሲሆን፣ በዋናነት ዓለማ ያደረገው ደግሞ “በማንኛውም ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቀሴ ውስጥ ለሚደረግ የነቃ ተሳትፎ ትምህርት ቁልፍ ጉዳይ ነው” የሚለውን መሠረተ ሃሳብ ነው። በ2013 (እ.ኤ.አ.) በፋዌ ኢትዮጵያ በኩል ወደተግባር የገባው ይህ ፕሮግራም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ መተግበር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ተማሪዎችን በተለያዩ የስኮላርሽፕ ጥቅል ድጋፎች አማካይነት መታደግ ችሏል። ሊጠናቀቅ በተቃረበው የፈረንጆቹ የ2021 ዓ.ም. በርካታ ተማሪዎችን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህም መሰረት፣ በፕሮግራሙ የእስካሁኑ ሂደት 800 ያህል ተማሪዎች (600 ሴቶች እና 200 ወንድ ተማሪዎች) የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አስኪያጠናቅቁ ድረስ ተጠቃሚ ሆነዋል፤ እየሆኑም ይገኛሉ። ፕሮግራሙ ጥራት ላለው ትምህርት ትኩረት የሚሰጥ እንደመሆኑ፣ በፕሮግራሙ ተጠቃሚ እየሆኑ ያሉ እነዚህ ተማሪዎች በሁለንተናዊ መልኩ ብቁ ዜጋ ሆነው ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ፕሮግራሙ፣ በባህርዳር፣ በአዳማ፣ በሃዋሳና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የተለያዩ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚገኙና የሥርዓተ ፆታ ክፍተት በሰፋት በሚስተዋልባቸው ስምንት ትምህርት ቤቶች በመተግበር ላይ ይገኛል። የዚህ ፕሮግራም የዓመቱ አበይት ክንውኖች የአፈፃፀም ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ✓ የፕሮግራሙ የ2020 ዓ.ም. ዓመታዊ የሥራ ክንውን የአፈፃፀም ሁኔታ የተገመገመበት እና በ2021 ዓ.ም. ሊሠሩ የታቀዱ ተግባራትን የሚያስተዋውቅ ዓመታዊ ጉባኤ በዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ላይ ተካሂዷል። በዚህ ጉባኤ ላይ፣ የፕሮግራሙ ባለድርሻ አካላት ፕሮግራሙ ከሚተገበርባቸው ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ 50 ያህል በፕሮግራሙ አፈፃፀም ላይ ቁልፍ አስተዋፅኦ ያላቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል። መምህራንን፣ ርእሳነመምህራንን፣ የትምህርት ባለሙያዎችን፣ የየወረዳውን የሴቶች፣ የህፃናትና የወጣት ጽ/ቤት ተወካዮችን እንዲሁም የኢኮኖሚና ልማት ቢሮዎችን እና የፋዌ ኢትዮጵያ አባላትንና ጥሪ የተደረገላቸውን እንግዶች ባካተተው በዚህ ጉባኤ ላይ፣ የፕሮግራሙ የ2020 ዓ.ም. ዝርዝር የአፈፃፀም ሪፖርት በፋዌ ኢትዮጵያ የፕሮግራም ክትትልና ግምገማ ክፍል ቀርቧል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በፕሮግራሙ የታቀፉ ተማሪዎችን የትምህርት አቀባበልንና በትምህርት አቀባበላቸው ላይም ተፅእኖ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን በሚመለከት በፕሮግራሙ ካልታቀፉ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ጋር በማነፃፀር የተካሄደው ጥናት ግኝት ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል።



የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ ፕሮግራም የእቅድ እና የአፈፃፀም ግምገማ ተሳታፊዎች

✓የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም መተግበር ከጀመረ ጊዜ አንስቶ ከሚተገበሩ ተግባራት መካከል አንዱ፣ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን ያሣተፉ ዓመታዊ ኮንፈራንስ ማካሄድ ነው። በዚህም መሰረት፣ የ2021 ዓ.ም. ዓመታዊ ኮንፈረንስ ከነሐሴ 4 - ነሐሴ 5 2021 ዓ.ም. ድረስ ቢሾፍቱ በሚገኘው የJeCC-DO የስልጠና ማእከል ተካሂዷል፣ ፣ 89 ተማሪዎችን (66 ሴቶች፣ 23 ወንዶች) ባሳተፈው በዚህ ዓመታዊ ኮንፈረንስ ላይ፣ በአመራር ክህሎት፣ በሥነተዋልዶ ጤና፣ በሌሎች ወጣቶችን በሚያጋጥሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። ባሀርዳር የሚገኙ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ተማሪዎችን ታሳቢ ያደረገ ተመሣሣይ ዓመታዊ ኮንፈራንስም ባሀርዳር በሚገኘው ጣና ሃይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተካሂዷል።

✓የማስተርካርድ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙን በስኬት ሲያጠናቅቁ፣ የሚካሄደው ዓመታዊ የምርቃት ሥነስርዓት በዚህ ዓመትም ተካሂዷል። ለ3ኛ ጊዜ በተካሄደው በዚህ ዓመታዊ የምርቃት ፕሮግራም ላይ ከትምህርት ሚኒስቴር የተጋበዙ እንግዶች፣ ፕሮግራሙ የሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች ርእሳነመምህራን፣ ለፕሮግራሙ ስኬት የበኩላቸውን ድርሻ እየተወጡ የሚገኙ መንግስታዊ አካላት ተወካዮች እና የፋቂ ኢትዮጵያ ቻፕተር የቦርድ አባላትና የቻፕተሩ ጽ/ቤት ሠራተኞች ታድመዋል፣ ፣ በዚህ የምረቃ ሥነስርዓት ላይ ከሁሉም ተመራቂ ተማሪዎች ውስጥ በትምህርታቸው የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ 6 ተማሪዎች ለአያንዳንዳቸው የላፕቶፕ ሽልማት ተበርክቷል። እንዲሁም፣ የፕሮግራሙ ትግበራ በሚከናወንባቸው ክልሎች ውስጥ ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ላስመዘገቡ ሌሎች 6 ተማሪዎችም ለአንዳንዳቸው የሞባይል ሽልማት ተሰጥቷል። በዚህ የምርቃት ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ላልቻሉ የባሀርዳር የስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች፣ ተመሳሳይ ፕሮግራም ባሀርዳር በሚገኘው ጃካራንዳ ሆቴል ተከናውኗል።



ከፍተኛ ውጤት ያመጣች የስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪ የላፕቶፕ ሽልማት ስትቀበል

✓ የፕሮግራሙ ተሳታፊ ለሆኑ 5 የጣና ሃይቅ ትምህርት ቤት ዓይነስውራን ተማሪዎች "Reader Assisted Computer Literacy" በሚል ርእስ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጥቷል። ለ18 ቀናት የተካሄደው ይህ ስልጠና፣ እ.ኤ.አ. ከግንቦት 19 - ሰኔ 5/2021 ከ"Network of Organizations for the Visually Impaired and the Blind (NOVIB)" ጋር በመተባበር የተካሄደ ሲሆን፣ በስልጠናው የማጠናቀቂያ ፕሮግራም ላይም የተባባሪ ትምህርት ቤቶች ተወካዮች እና የሚመለከታቸው የአማራ ክልል የሥራ ሃላፊዎች ታድመዋል። በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይም፣ በስልጠናው ተሳታፊ ለሆኑ ተማሪዎች ሁሉ የላፕቶፕ ሰጦታ ተበርክቶላቸዋል።

✓በሜንተርነት የሚሳተፉና ከአዳማ፣



የስልጠና ተሳታፊ የጣና ሃይቅ ዓይነስውራን ተማሪዎች

ከሃዋሳ፣ ከባሀርዳር እና ከአዲስ አበባ ለተውጣጡ 11 መምህራን፣ የሜንተርነት ሥራቸውን አስመልክቶ ያስተዋሏቸው ጉዳዮች በተመለከተ ከተለያዩ የትምህርት ባለሙያዎች ጋር ተወያይተዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ኮቪድ-19ን በመከላከል ሂደት ባጋጠማቸው ጉዳዮች ዙሪያ ላይም ውይይት አካሂደዋል። ሜንተሮቹ፣ ያካሄዱትን ውይይት እና በውይይታቸው ሂደትም በተወያዮች ላይ ያስተዋሏቸውን ሁኔታዎች የተመለከተ ዝርዝር ሪፖርትም አቅርበዋል።

✓ሥነልቦናዊ የመጀመሪያ እርዳታ እና አዎንታዊ ሥነምግባር (Psychological First and Positive Discipline) በሚል ርእሰ ጉዳይ ላይ "IMPACT Psychological and Health Services Consulting PLC" በተሰኘ የምክር አገልግሎት ሰጪ ድርጅት አማካይነት ፕሮግራሙ ከሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ 18 (8 ሴቶች፣ 10 ወንዶች) የትምህርት ቤት የምክር አገልግሎት ሰጪዎችእና ሜንተሮች (School Counsellors and Mentors ቢሾፍቱ በሚገኘው JeCDO የስልጠና ማእከል እ.ኤ.አ. ከነሐሴ 4 - ነሐሴ 8 2021 ዓ.ም. ተካሂዷል፣ ፣ እንዲሁም፣ የአንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ማሳደጊያ ስልጠና ከአዳማና ከሃዋሳ ለተውጣጡ የ4ኛ እና የ5ኛ ዙር የስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች በተመሳሳይ መልኩ ተሰጥቷል። ይህን ስልጠና የሰጡት፣ "Albert Institute, Divine Sparks, $H_2O$ and Galaxy" የተሰኙ የቋንቋ ስልጠና ማእከላት ናቸው። በእነዚህ ስልጠናዎች በአጠቃላይ 183 (120 ሴቶችና 63 ወንዶች) ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ተሳትፈዋል። በተጨማሪም፣ በሁሉም ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ተጠቃሚ ተማሪዎች፣ በሥራ ፈጠራ/Entrepreneurship፣ በህይወት ክህሎት እና በአይሲቲ ዙሪያ የስልጠና ፕሮግራሞች ተካሂደዋል። "Digital Op-

portunity Trust (DOT)" በተሰኘ ተቋም አማካይነት በተሰጡት በእነዚህ ስልጠናዎች 181 (130 ሴቶች፣ 51 ወንዶች) ተሳትፈዋል፡፡

✓የፕሮግራሙ የሁለተኛው የ5 ዓመት ፕሮግራም ከተጀመረ በኋላ፣ የፕሮግራሙን የአፈፃፀም ሁኔታን የተመለከተ የመካከለኛ ጊዜ የሥራ አፈፃፀም ሂደት ግምገማ (Mid-Term Review) የፋዌ ኢትዮጵያ እና ቁልፍ የሆኑ የፕሮግራሙ ባለድርሻ አካላትና ተባባሪ አካላት በተገኙበት ተከናውኗል፡፡ ግምገማው፣ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች በአካል በመገኘት፣ እ.አ.አ. ነሐሴ 13 ቀን 2021 ዓ.ም. በአዲስ አበባ፣ ነሐሴ 17 ቀን 2021 በአዳማ፣ ነሐሴ 26 ቀን 2021 ደግሞ በባህርዳር ተካሂዷል፡፡ በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት በተካሄዱት የሥራ አፈፃፀም ምልከታዎች ላይ፣ ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙባቸው ክልሎችና የክተማ አስተዳደር ተወካዮችና የፋይናንስ እና የትምህርት ቢሮ የሥራ ሃላፊዎች፣ የተባባሪ ትምህርት ቤቶች ርእሳነ መምህራን ተሳትፈዋል፡፡

✓ለአብዛኞቹ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ተማሪዎች የቱቶሪያል ፕሮግራም ተመቻችቶ ተተግብሯል፡፡ ሁሉም ተጠቃሚ ተማሪዎች በቱቶሪያል ፕሮግራሙ በንቃት እንዲሳተፉ ያልተቋረጠ ክትትል ተደርጓል፡፡ የቱቶሪያል ፕሮግራሞቹ ከመተግበራቸው በፊትም ተማሪዎቹ በትምህርት አቀባበላቸው ያሉበትን ደረጃ ማወቅ እንዲቻል ቅድመ ቱቶሪያል ምዘና (Pre Tutorial Exam) በሁሉም ትምህርት ቤቶች በየክፍል ደረጃው ተካሂዷል፡፡ ቅድም ምዘናው፣ በምዘናው የተገኘውን ውጤት በድህረ ቱቶሪያል በሚሰጠው ምዘና ከሚገኘው ውጤት ጋር የተማሪዎችን ውጤት ማነፃፀር የሚቻልበትን መረጃ ለማግኘት ታስቦ የተካሄደ ነበር፡፡

✓ በፕሮግራሙ የአፈፃፀም ሂደት፣ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ ተጠቃሚ ተማሪዎች መካከል፣ ለተለያዩ ህመሞች የተጋለጡና ቤተሰቦቻቸው ባላቸው የአቅም ውስንነት የተነሳ ተገቢውን የህክምና ወጪ ሊሸፍኑላቸው የማይችሉ 12ተማሪዎችን በመለየት፣ ከሚደረግላቸው የትምህርት ድጋፍ በተጨማሪ የህክምና ወጪ ድጋፍም ሊደረግላቸው ችሏል፡፡

✓በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ተማሪዎች ዘንድ የተለመዱ የአእምሮ መታወክ የመከሰታቸውን ሁኔታ፣ እንዲሁም የሚያስከትሏቸውን የተለያዩ ጉዳቶችንና ተፅእኖዎችን በተመለከተና በመምህራን ዘንድም ስለህመሞቹ ተገቢው ግንዛቤ ስለመኖሩ ማወቅ የሚያስችል ጥናት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ከኢምፓክት ኢትዮጵያ የሥነልቡና አገልግሎትና እና የህብረተሰብ ጤና የምክር ተቋም ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ፣ 118 ተጠቃሚ ተማሪዎችን እና ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ 16 መምህራንን እና 8 ርእሳነ መምህራንን ያሳተፈ ነበር፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረትም፣ 25.4% የሚሆኑ ተማሪዎች ላይ ችግሩ እንደሚስተዋል እና መምህራንም ስለችግሩ ያላቸው ግንዛቤን አነስተኛ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ የጥናቱ ውጤትም፣ ከትምህርት ሚኒስቴር የተወከሉ ባለሙያዎች፣ እንዲሁም፣ ፕሮግራሙ የሚተገበርባቸው የክልል እና የወረዳ የተለያዩ ቢሮዎች ተወካዮችና ሌሎች ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ ከሚተገበርባቸው 8 ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡና የሥነልቡና ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት ለሚያስፈልጋቸው 24 ተጠቃሚ ተማሪዎች አገልግሎቱ ተሰጥቷል፡፡ አገልግሎቱ የተሰጠውም፣ ኢምፓክት ኢትዮጵያ የሥነልቡና አገልግሎትና እና የህብረተሰብ ጤና የምክክር ተቋም ከተሰኘ ሃገር በቀል የምክር አገልግሎት ሰጪ ተቋም በመጡ ባለሙያዎች ሲሆን፣ በስልጠናው ሂደትም ተጨማሪ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል የተባሉ የተወሰኑ ተማሪዎች ተለይተው ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

✓በፕሮግራሙ ተሳታፊ በሆኑ ተጠቃሚ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን የተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል። የዳሰሳ ጥናቱ፣ በተለየ ሁኔታ ትኩረት ያደረገው፣ በትምህርት አቀባበላቸው ድክመት ይታይባቸዋል በተባሉ ተማሪዎች ላይ ነበር፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደጠቆመው፣ በተጠቃሚ ተማሪዎች ዘንድ ለሚስተዋለው ዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል የተለያዩ ጉዳዮች ድርሻ ይኖራቸዋል፡ ፡ ከእነዚህም መካከል፣ ተጠቃሚ ተማሪዎች በሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የግብዓቶች አለመሟላት እና የመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍት እጥረት መኖር በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ጥናቱ በተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ላይ ከትምህርት ቤት የሚኖር የመኖሪያ ቤት ርቀት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የሚኖር ዝቅተኛ ተሳትፎ፣ ከትምህርት ቤት መቅረት፣ በራስ የመተማመን መንፈስ ማነስ፣ የጥናት ክህሎት (Study Skill) ላይ የሚታይ ችግር፣ የወላጆች ከትምህርት ጋር ያላቸው ቅርበት አነስተኛ መሆን እና በትምህርት ቤቶች የአቻዎች (Peers) ተፅእኖ መኖር የበኩላቸውን ተፅእኖ ማድረጋቸውን ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ምዘናው፣ እነዚህን ችግሮች መቅረፍ ለተማሪዎች የትምህርት አቀባበል የሚኖረውን አስተዋፅኦ መሰረት በማድረግ፣ ሊከናወኑ ይገባቸዋል ያላቸውን ተግባራትንም ጨምሮ ጠቁሟል፡፡



**በሥራ ፈጠራ፣ በህይወት ክህሎት እና በአይሲቲ ዙሪያ የተሰጡ ስልጠናዎች ተሳታፊዎች**



## Beyond numbers towards Gender Transformation” ፕሮጀክት

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከትምህርት ቤቶች ውጪ ማህበረሰብ አቀፍ የተለያዩ ፕሮግራሞችንም ያከናውናል። ከእነዚህ ውስጥ፣ ከብሪትሽ ካውንስል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እና በፕሮ ፕራድና አጋሮቹ ትብብር የሚከናወነው ማህበረሰብ አቀፍ ፕሮግራም አንዱ ነው። ከዚህ አኳያም፣ Civil Society Support Program (CSSP II) በመባል የሚታወቀው የዚህ ፕሮግራም አካል የሆነው “Beyond Numbers: Towards Gender Transformation” የተሰኘው ማህበረሰብ አቀፍ ፕሮጀክት በዋናነት ይጠቀሳል። ይህ ፕሮጀክት፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደብረ ብርሃን ከተማ በሚገኙ 5 ቀበሌዎች እና በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሸኖ ከተማ በሚገኙ 2 ቀበሌዎች፣ እንዲሁም በአሌልቱ ከተማ 1 ቀበሌ ውስጥ በመተግበር ላይ ይገኛል፡ ፡ ፕሮጀክቱ በዋናነት ከሥርዓተ ፆታ ጋር በተያያዘ ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ የሚያተኩር ሆኖ፣ የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በማሳደግ የውሳኔ ሰጪነት አቅማቸውን የማጎልበት እና ፆታዊ ጥቃትን የመከላከል ብቃታቸውን ማሳደግ ላይ መሰረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል። በዚህም መሰረት፣ ፕሮጀክቱ ሥራ ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። በዓመቱም የሚከተሉት ተግባራት ዋናዎቹ ናቸው።

✓ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው አካባቢዎች፣ ሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፏቸውን የበለጠ ማሳደግ እንዲችሉ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ፣ ቀበሌዎቹ ከሚገኙባቸው ወረዳዎች የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች ቢሮዎች ጋር በመተባበር ተካሂዷል። በመድረኩ ላይም፣ 120 የሚሆኑ በሴቶች መብት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አባላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን፣ መድረኩ የተሳታፊዎችን ብሄራዊና አካባቢያዊ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን የመገንዘብ አቅም በማጎልበት ረገድ አይነተኛ ሚና የተጫወተ ስለነበር፣ ተሳታፊዎች በወቅቱ ይካሄድ በነበረው ሃገራዊ ምርጫ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጎ ነበር ማለት ይቻላል።

✓በመጀመሪያዎቹ ሁለት የፕሮጀክቱ የሩብ ዓመት እቅድ መሰረት፣ የተለያዩ የሬዲዮ ፕሮግራሞች የተላለፉ ሲሆን፣ ፕሮግራሞቹ በዋናነት ትኩረት ያደረጉት በሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎ፣ በፆታዊ ጥቃት እና በሴቶች የውሳኔ ሰጪነት ችሎታ መጎልበት ላይ ነበሩ። የሬዲዮ ፕሮግራሞቹ በተለያዩ ስልቶች የቀረቡ በመሆናቸው፣ የፕሮጀክቱን ዓላማዎች በማስጨበጥ ረገድ የበኩላቸውን ሚና መጫወት በመቻላቸው፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የመነቃቃት ስሜት ሊፈጠር ችሏል፡ ፡ ከዚህ የተነሳም፣ አሌልቱ ወረዳ አካባቢ ከ23 ቀበሌዎች የተውጣጡ የህብረተሰብ ክፍሎች (ታዋቂ ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የመንግስት የሥራ ሃላፊዎች) በአካባቢው የሚስተዋሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በሚመለከት መወሰድ በሚገባቸው ርምጃዎች ዙሪያ ምክክር በማድረግ፣ አካባቢ ተኮር ባህላዊ የሀግ ድንጋጌን ማውጣት ችለዋል፡ ፡ ባህላዊ ህጉንም የወረዳው ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ቢሮም በመቀበል ሥራ ላይ እንዲውል የሚያስችል ተግባራዊ እንቅስቃሴ አድርጓል።



የማህበረሰብ አቀፍ ፕሮግራም የደብረብርሃን ነዋሪዎች በውይይት ላይ

✓ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው ወረዳዎች ውስጥ በተለያየ መልኩ በባለድርሻነትና በተባባሪነት ተሳትፎ የሚያደርጉ አካላት፣ የፕሮግራሙን የአፈፃፀም ሁኔታ የተመለከተና የልምድና የመረጃ መለዋወጫ በመሆን ያገለገለ መድረክ ተመቻችቶ ተግባራዊ ሆኗል። መድረኩ፣ ለሶስት ጊዜያት ያህል የተካሄደ ሲሆን፣ ከመድረኮች ተሳታፊዎች እንደተጠቆመው፣ መድረኮቹ ስለፕሮጀክቱ ዓላማ እና በሴቶች ላይ በሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤ በማስፋት፣ እንዲሁም ያሉባቸውን ክፍተቶች በመሙላት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

✓ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው ቀበሌዎች ሁሉ፣ ለፕሮግራሙ በስኬት መተግበር የበኩላቸውን ሚና የሚጫወቱ የአማካሪ ቡድኖች ተቋቁመዋል። የአማካሪ ቡድኖቹ መቋቋም፣ ፕሮጀክቱ በእቅዱ መሰረት ተግባራቱን እንዲያከናውን አገዛ አድርጓል። በተለይም፣ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች በተለያየ መልኩ ለመደገፍ የሚያስችሉ ስልቶችን ቀይሶ በመንቀሳቀስ ረገድ የነበረው ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ፣ በየቀበሌዎቹ እነዚህን ጥቃቶች የተመለከቱ አገልግሎቶች ተዘርግተው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መካሄድ ችሏል። ከአገልግሎቶቹ መካከልም፣ ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች፣ የህግ እና ከጤና ጋር የተያያዙ ምክሮችን መስጠት፣ የገንዘብና የምግብ አቅርቦት ማመቻቸት የሚሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

## “Malala Foundation Global COVID-19 Initiative” ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት፣ ፋዌ ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (NEWA) ኮቪድ-19 በሴቶች ትምህርት ላይ ያስከተለውን ተፅእኖ እና ተፅእኖውንም ለመቅረፍ መወሰድ ባለባቸው ርምጃዎች ላይ ያተኮረ ነው። ፕሮጀክቱ እ.ኤ.አ. 2021 መጀመሪያ በሁለቱ አካላት በተደረገ ስምምነት መተግበር የጀመረ ሲሆን፣ ለ18 ወራት አዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚተገበር ነው። ፕሮጀክቱ የሚተገበረው በ10 ትምህርት ቤቶች ሲሆን፣ እነዚህም ትምህርት ቤቶች የሚገኙት በአዲስ ከተማ (5 ትምህርት ቤቶች) እና በኮልፌ ቀራኒዮ (5 ትምህርት ቤቶች) ክፍለ ከተሞች ነው። የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ፣ ኮቪድ-19 በሃገራችን መሰራጨት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በሴት ተማሪዎች ላይ በተለያየ መልኩ እያደረሰው ያለውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫናዎችን መቀነስ የሚያስችሉ ርምጃዎች ነቅሶ በማውጣት፣ ሴት ተማሪዎች ጫናውን በመቋቋም በትምህርታቸው እንዲገፉ ማድረግ ላይ ያተኮረ ነው።

በዚህ የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ መሰረት፣ የተለያዩ ዝርዝር ዓላማዎችን በመቅረፅ፣ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ መሆን የጀመረ

ሲሆን፣ ከተቀረፁት ዝርዝር ዓላማዎች መካከልም፣ በመንግስት በኩል ለሴቶች ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት እንዲሻሻል ለማድረግ የሚያስችል ጉትጎታ ማድረግ፣ በበሽታው ምክንያት ጫና ውስጥ ለወደቁ ሴት ተማሪዎች አማራጭ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ፣ ከትምህርት ገበታቸው የራቁ ተማሪዎችን ወደትምህርት ገበታቸው መመለስ፣ የባከነውን የትምህርት ጊዜ ማካከስ የሚያስችል አሠራር መቀየስ፣ ለሥርዓተ ፆታ ምላሽ የሚሰጥ እና ፍትሃዊነት ላይ የተመሰረተ የትምህርት ሥርዓት በኮቪድ-19 ምክንያት የተዘጉ ትምህርት ቤቶች በሚከፈቱበት ወቅትና ወደሙሉ የትምህርት ስርዓት ሲገቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው። በእነዚህ ዋናና ዝርዝር ተግባራት እና በፕሮጀክቱ እቅድ መሰረትም፣ የተለያዩ ተግባራት በዓመቱ ተከናውነዋል። የተግባራቱ አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

✓ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ የወረዳ የትምህርትና የህግ አስፈፃሚዎች፣ እንዲሁም የየትምህርት ቤቶቹ ርእሳነ መምህራን የፕሮግራሙን ዓላማ የተመለከተ የምክክር መድረክ፣ ሚያዚያ 23 ቀን 2021 ዓ.ም. 19 ባለሙያዎችን በማሳተፍ ተካሂዷል። የምክክር መድረኩ፣ ኮቪድ-19 በሴቶች ትምህርት ላይ በተለይ እያስከተለ ያለውን ተፅእኖና ጫና የተመለከተ ገለፃ የተሰጠበትና በገለፃው መሰረትም የሃሳብ ልውውጥ የተካሄደበት ነበር። የውይይት መድረኩ ተሳታፊዎች በሰነዘሯቸው አስተያየቶች፣ የወረርሽኙን ተፅእኖ ለመቀነስ እና በቀጣይም ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ርምጃዎች ጠቃሚ የሆኑ ሃሳቦችን አቅርበዋል። በተለይም፣ ኮቪድ-19 በተለያየ መልኩ እያስከተለ ያለውን ተፅእኖ መቋቋም እንዲቻል፣ የሚመለከታቸው አካላትም ሆኑ ህብረተሰቡ የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ እንዳለባቸው በአፅንኦት ተጠቁሟል፤ የጋራ ስምምነትም ላይ ተደርሷል።

✓በተመሳሳይ ኮቪድ-19 በሃገራችን ላይ በፈጠረው ጫና የተነሳ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ መደረጉ፣ በትምህርት ስርዓቱ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የፈጠረውን መስተጓጎል መቅረፍ እንዲቻል፣ መወሰድ ባለባቸው ርምጃዎች ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ የአንድ ቀን ውይይት በአዲስ ከተማ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተካሂዷል። ሚያዚያ 28 ቀን 2021 ዓ.ም. በተካሄደው በዚህ ውይይት ላይ፣ ፕሮግራሙ ከሚተገበርባቸው ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ርእሳነመምህራን፣ ዩኒት መሪዎች፣ እንዲሁም የወላጆች መምህራንና ተማሪዎች ጥምረት ተወካዮች፣ የልጃገረድ ክበባት እና የሴት መምህራን ተወካዮች ተሳታፊ ሆነዋል። 40 ተሳታፊዎች የታደሙበትን ይህን የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት፣ በትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ፆታ ባለሙያ የሆኑት አቶ ብርሃኑ አረጋ ሙያዊ ገለፃ በመስጠት የመሩት ሲሆን፣ ተሳታፊዎችም የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅና የተለያዩ አስተያየቶችን በመሰንዘር የነቃ ተሳትፎ አድርገዋል። በተለይም፣ መንግስት የወረርሽኙን መስፋፋት ለመግታት በወሰደው ርምጃ ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ በኋላ ዳግም በሚከፈቱበት ወቅት እንደገና በተካሄደው ዳግም ምዘገባ ወቅት ያስተዋሏቸውን ሁኔታዎች በሚመለከት ተሳታፊዎች ተጨባጭ መረጃዎችን በመንተራስ ባቀረቧቸው አስተያየቶች መነሻ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል።

✓በፕሮግራሙ ዓላማ መሰረት ከታቀዱ ተግባራት መካከል አንዱ፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ አቅም መገንቢያ ስልጠናዎችን ማካሄድ ነው። በዚህም መሰረት፣ ፕሮግራሙ ከሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ የልጃገረዶች ክበባት ተወካዮች፣ ከአመራር ጥበብ፣ ራስን ከመምራትና ከሜንቶር ጋር የተያያዙ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል።



ኮቪድ-19 በሴቶች ትምህርት ላይ ባሳደረው ተፅእኖ ዙሪያ የተካሄደ ምክክር ተሳታፊዎች

✓16 ቀናት የሚቆይ እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶችን በተመለከተ ግንዛቤ በመፍጠር፣ በመከላከል ላይና ከናካቴውም እንዳይኖሩ በማድረግ ላይ ያተኮረ "ዓለም ዓቀፍ የፀረ ፆታዊ ጥቃት ቀን" በየዓመቱ ይከበራል። ቀኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ህዝቡን የማንቃት ዘመቻ ሆኖ እንዲከበር፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀኑ እንዲታወስ እ.ኤ.አ. 1991 ላይ ሃሳቡን ያመነጨው፣ የዓለም አቀፉ የሴቶች የአመራር ማእከል አካል የሆነው የሴቶች ዓለም አቀፍ የአመራር ኢንስቲትዩት የተሰኘው ድርጅት ነው። "16ቱ የፀረ ፆታዊ ጥቃት ቀን" በሚል ርእስ ለ16 ቀናት በዘመቻ መልክ የሚካሄደውና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶች እንዲወገዱ ዋና ግቡ/መዳረሻው ያደረገው ይህ ዘመቻ፣ እ.ኤ.አ. ከህዳር 25 እስከ ታህሣስ 10 ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ሀገራት በተለያየ መልኩ ይከበራል። ቀኑ ለ16 ቀናት ሲከበር የመጨረሻው የመጠናቀቂያ ቀን፣ የሆነው ታህሣስ 10 ቀን "የሰብዓዊ መብት"

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበርበት እንደመሆኑ፣ ከዚሁ ከሰብዓዊ መብት ጋር ተቀናጅቶ ይከበራል። ቀኑ በቅንጅት ከሰብዓዊ መብት ቀን ጋር ተቀናጅቶ መከበሩ፣ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶች የሰብዓዊ መብት ጥሰት አካል መሆናቸውንና የተሰሩ መሆናቸውን ተምሳሌታዊ አድርጎ ለማመልከት ነው። ከዚሁ ከሰብዓዊ መብት በተጨማሪ፣ በዚሁ 16 ቀን ወስጥ ሌሎችም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ በተለያዩ ስያሜዎች የሚከበሩ ቀናትም አሉ። በዚህም መሰረት፣ እ.ኤ.አ. ህዳር 29 ቀን "ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ሰብዓዊ መብት ተከላካዮች ቀን" ፣ ታህሣስ 1 ቀን "የኤድስ ቀን"፣ ታህሣስ 3 ቀን "የአካል ጉዳተኞች ቀን"፣ ታህሣስ 6 ቀን "የሞንቲሪያል ፍጅት/ አልቂት መታሰቢያ ቀን" እና ታህሣስ 10 "የሰብዓዊ መብት ቀን" በመባል ታስበው የሚውሉት ቀናት ተጠቃሽ ናቸው። "የ16ቱ የፀረ ፆታዊ ጥቃት ቀን" በየዓመቱ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መከበሩ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በግልም ሆነ በተቋም ደረጃ በሴቶች ላይ የሚደርሱ

ሁሉንም ዓይነት ዶታዊ ጥቃቶችን ከእናካቴው እንዲወገዱ/እንዲጠፉ የሚያስችሉ የተለያዩ የአሠራር ስልቶችን ለመቀየስ በእጅጉ ጠቅሟል፡ ፡ በዚህም መሰረት፣ ፋዌ ኢትዮጵያና ሌሎች በሴቶች ሃገራዊ ሁለንተናዊ ተሳትፎ፣ መብትና ጥቅም ዙሪያ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉ አካላት፣ የፀረ ዶታዊ ቀኑን በየዓመቱ በድምቀት የተለያዩ መርሃግብሮችን በማዘጋጀትያከብሩታል።

የ2014 የ16ቱ የፀረ ዶታዊ ጥቃት ቀንም፣ "ሰላም ይስፈን፣ በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚደርስ ጥቃት ይቁም!" በሚል መርህ በሃገራችን የተከበረ ሲሆን፣ ይህንን መርህ መሰረት በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በፋዌ ኢትዮጵያ አዘጋጅነት በዐውደጥናት በማካሄድ ታስቦ ውሏል፡ ፡ አለቱን አስመልክቶ የተዘጋጀው ዐውደ ጥናትም፣ በስርዓተ ዶታ ጉዳዮች ዙሪያ በባለሙያነታቸው በሚታወቁት በወ/ሮ አልማዝ አወያይነት፣ ታህሣስ 6 ቀን 2014 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው አዘመን ሆቴል ተካሂዷል።

# "The Break Free" ፕሮጀክት

በፋዌ ኢትዮጵያ አማካይነት ከሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ፣ "The Break Free" በሚል ስያሜ የሚታወቀው ፕሮጀክት ነው። ይህ ፕሮጀክት፣ በፕላን ኢንተርናሽናል ኔዘርላንድ፣ በአህጉራዊው ፋዌ ጽ/ቤት እና በሌሎች ተባባሪ አካላት፣ እንዲሁም ለፕሮጀክቱ ቴክኒካዊ ድጋፍ በሚያደርጉ ድርጅቶች የጋራ ትብብር የሚካሄድ ነው። የትብብር ፕሮጀክቱ በዋናነት፣ በስነተዋልዶ ጤና፣ በሥርዓተ ዶታ እኩልነት፣ በወጣቶች፣ በሴቶችና በልጃገረዶች ጤንነት ጥበቃ እና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ በተለይም ወጣት ሴቶች ከልጅነት እርግዝና ርቀው እና ካለአድሜ ጋብቻ ራሳቸውን ጠብቀው የመኖር ሙሉ ነፃነት እንዳላቸው፣ ይህንንም ነፃነት ጠብቀው የመኖር መብታቸውን እንዲያስቀጥሉ ድጋፍ የመስጠት ዓላማን ያነገበ ነው፡ ፡ ፕሮግራሙ መተግበር የጀመረው ጥር 2021 ዓ.ም. ሲሆን፣ በሆላንድ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የገንዘብ ድጋፍ ይደረግለታል።

በፕሮግራሙ ዓላማ መሰረት፣ በ2021 ዓ.ም. የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። በዚህም መሰረት፣

- ✓ ለፕሮግራሙ ስኬታማ አፈፃፀም አስቻይ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራ ከማከናወን አንፃር፣ ፕሮጀክቱ ሊተገበርባቸው የሚችሉ ስፍራዎችን የመምረጥ ሥራ ፕሮጀክቱን በስኬት ለማጠናቀቅ አገዛ ከሚያደርጉ የመንግስት አካላት ጋር በመቀናጀት ተከናውኗል። የፕሮጀክቱን ዓላማ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የማስተዋወቅ እና በዓመቱ በፕሮጀክቱ አቅድ መሰረት የተካሄዱ ተግባራትን የአፈፃፀም ሁኔታ የተመለከተ ግምገማም ተካሂዷል። ከዚህ በተጨማሪ፣ በቀጣይ በልጃገረዶች ትምህርት ዙሪያ የተቀረፀ ህጎችና ፖሊሲዎች ያሉበትን ሁኔታና አተገባበራቸውን፣ እንዲሁም ለስርዓተ ዶታ እኩልነት የሚደረገውን ድጋፍ እና ሌሎችንም ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ ጥናት እንዲያካሂዱ ከሶስት ሃገር በቀል የምክር አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት ጋር ስምምነት ላይ ተደርሷል።
- ✓ ከሴቶች ትምህርት አኳያ የሚቀረፁ ፖሊሲዎችን፣ የልማት አቅዶችና የሚመደብ በጀት የተመለከቱ መረጃዎችን ማደረጃት እና ትንተና ማካሄድ፣ የተቀረፁ ህጎች መኖራቸውንና መተግበራቸውን እንዲሁም የሀብት ድልድሉ ሥርዓተ ዶታን ያማከለ መሆኑ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በሃገር አቀፍ ደረጃ ያሉበትን ደረጃ የተመለከተ የተገቢነት/የትክክለኛነት ዐውደጥናት ታህሣስ 9 ቀን 2014 ዓ.ም አዲስ አበባ በሚገኘው ኢ.ኤ.ሌ ሆቴል ተካሂዷል። በዐውደጥናቱ ላይ ከመንግስት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተውጣጡ ተወካዮችና የፋዌ ኢትዮጵያ እና የፋዌ ኢትዮጵያ ተባባሪ የሆነው የPIE ባለሙያዎች፣ በአጠቃላይም 20 ተሳታፊዎች ታድመዋል። የተገቢነት/የትክክለኛነት ዐውደጥናቱ ዋና ግብ/ዓላማ የሴቶች ትምህርትን በተመለከተ የተቀረፁ ህጎች እና ፖሊሲዎች በሚገባው መጠን መካተታቸውንና ሥራ ላይም መዋላቸውን መፈተሽ፣ ለሥርዓተ ዶታ እኩልነት መረጋገጥም ተገቢው በጀት መመደቡን ማረጋገጥ እና በዚህ ረገድም በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ ያለውን ሥርዓተ ዶታን በተመለከተ የተቀረፁ ፖሊሲዎች ወቅቱን ባገናዘበ ሁኔታ ተገቢው ማሻሻያ እንዲደረግባቸው በማድረግ በኩል በባለድርሻ አካላት ዘንድ የሚስተዋለውን ክፍተት በመለየት ላይም ያተኮረ ነው። እንዲሁም የተገቢነትና የትክክለኛት ዐውደጥናቱ፣ ያሉትን ፖሊሲዎች፣ የልማት አቅዶች (በተለይም አየተተገበረ ካለው የESDP VI መርሃግብር ) በጀት ከሥርዓተ ዶታ አኳያ መፈተሽ በሃገር አቀፍ ደረጃ ተገቢዎቹን ተቋማትና ፖሊሲ ተግባሪዎችን መተንተንና ለይቶ ማደራጀት ፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የፖሊሲ ሰነዶችን ለማዘጋጀትና ለማሰራጨትና ለጉዳዩም ወትዋች/ጎትጓች እና ተከራካሪ ለመሆን፣ እንዲሁም ይህን በተመለከተ ለተካሄዱ ሁለት ጥናቶች መነሻ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል/ይገመታል። ከዐውደጥናቱ መጠናቀቅ በኋላ፣ የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎች፣ የቀረበውን ጥናት የሚያዳብሩ ጠቃሚነት ያላቸውን አስተያየቶች ሰንዝረዋል። በአለቱ ከዐውደጥናቱ መጠናቀቅ በኋላ፣ የሥርዓተ ዶታ እኩልነትን በተመለከተ ሊከናወኑና ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ጉዳዮችን የተመለከተ የፖሊሲ አጭር መግለጫ እና ማጠቃለያ (Policy Brief) የተመለከተ ሰነድ ለተሳታፊዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።
- ✓ ሌላው በዚህ ፕሮጀክት በዓመቱ ከተካሄዱ ዐውደጥናቶች አንዱ ትምህርት ለጤንነትና ደህንነት



"The Break Free" ፕሮጀክት የትውውቅ ፕሮግራም

የሚለውን አሳቤ በትምህርት ፖሊሲዎች እና ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ከማካተትና ከመተግበር አኳያ ያለበትን ደረጃ / ሁኔታ በሚመለከት የተካሄደ የተገቢነት ዐውደጥናት (Validation Workshop) ነው። ይህ ዐውደጥናት፣ አዲስ አበባ በሚገኘው አዘመን ሆቴል ተካሂዷል። በዚህ የተገቢነት ዐውደጥናት በአጠቃላይ 13 (5ቱ ሴቶች ናቸው) ከትምህርት ለጤናና ደህንነት ቴክኒካዊ ግብረሃይል፣ የሥራ ቡድን ፣ ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተውጣጡ ተወካዮች እና የፋዊ ኢትዮጵያና የPIE ባለሙያዎች ተሳትፈዋል። የዚህ ዐውደጥናት ዋና ግብ፣ ትምህርት ለጤንነትና ደህንነት የሚለው አሳቤ በትምህርት ፖሊሲውና በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ እንዲሁም በተለያዩ ፖሊሲዎች ውስጥ ከመካተት ባለፈ በትግበራ ደረጃ ያለበትን ሁኔታ መፈተሽና በትግበራ ሂደትም በሃገር አቀፍ ደረጃ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን መመርመር ላይ በዋናነት ያተኮረ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ፣ በሥርዓተ ትምህርቱም ሆነ በትምህርት ፖሊሲው ውስጥ ጉዳዮችን በተመለከተ መሻሻል የሚገባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ የመፍትሄ ሃሳብ የማፍለቅ ዓላማም የነበረው ዐውደጥናት ነበር። ለዐውደጥናቱ የቀረበው መነሻ ሃሳብ ጥናቱን ባዘጋጀው አማካሪ ድርጅት ተወካይ አማካይነት ተገቢው ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ፣ የዐውደጥናቱ ዓላማ ናቸው ተብለው ከተዘረዘሩ ጉዳዮች አኳያ የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎችም የበኩላቸውን ግብረመልስ እና አስተያየት በመስጠት የጥናቱን ግኝቶች ተገቢነት አረጋግጠዋል፣ ፣ እንደሚታወቀው፣ በትምህርት ለጤንነትና ደህንነት ውስጥ የሥርዓተ ፆታ ጉዳዮች ለስሜት ቅርብ (Sensitive Issue) እንደመሆናቸው፣ በግልፅ ለመነጋገር የራሳቸው ተፅእኖ ያለቸው ናቸው። ሆኖም፣ በእለቱ የተካሄደው ዐውደጥናት፣ እነዚህን ጉዳዮች ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር አስማምቶ መተግበር በሚቻልበት ሁኔታ የመንግስት ተቋማት ተወካዮችና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት መወያየት የተቻለበትን እድል የተመቻቸበት ነበር ማለት ይቻላል።

## “Make Way” ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት፣ ከጥር 2021 ዓ.ም. ጀምሮ በመተግበር ላይ ያለ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ፣ የአምስት ዓመት የቆይታ ጊዜ የሚኖረው ሲሆን፣ ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሚተገበር ነው። ከግብረሰናይ ድርጅቶቹ መካከልም፣ “Akina Mama Wa Africa (AMwA)፣ Liliane Foundation (LF)፣ VSO Netherlands” እና ሌሎች አጋር የሆኑ ድርጅቶች ተጠቃሽ ናቸው። “Make Way” የተሰኘው ይህ ፕሮጀክት በዋናነት የሚያተኩረው፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በወጣቶች ወሲብና የስነተዋልዶ ጤና ዙሪያ የበኩላቸውን ዓይነተኛ ሚና እንዲጫወቱ በማድረግ ላይ ነው። ከዚህ በተጨማሪም፣ የወጣቶች ዋና ችግር ናቸው ተብለው ከሚቆጠሩ ከእነዚህ ችግሮችና ከሌሎች ተያያዥ ችግሮች አኳያ ይበልጥ ተጋላጭ ናቸው በሚባሉት የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ በተለይ ሁኔታ ትኩረት በመስጠት የሚተገበር ይሆናል። በመሆኑም፣ እነዚህ ተማሪዎች ከወሲብና ከሥነተዋልዶ ጤና ችግሮች ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ሁኔታዎችን በተመለከተ የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማመቻቸት፣ በጉዳዮቹ ዙሪያም በነፃነት የሃሳብ ልውውጦች የሚካሄዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ክህሎትን ማዳበር እና የተገኙ ተሞክሮዎችን ሥራ ላይ በማዋል በኩል መንቀሳቀስ፣ የፕሮጀክቱ ዋና ተግባራት ናቸው።

## “Bearers of Life” ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት፣ “The Bearers of Life: Championing Women’s and Girls’ Right” የሚል ስያሜ የያዘ ሲሆን፣ በብሪቲሽ ካውንስል የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወንና “Civil Society Support Program” የሚለው ፕሮጀክት ሁለተኛ ክፍል ነው። ይህ ፕሮጀክት፣ “Beyond Numbers: Towards Gender Transformation” በሚል ሲተገበር እንደቀየው ቀዳሚው ፕሮጀክት ሁሉ፣ ፕሮፐራይድ በተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ትብብር በአማራ ብ/ክ/ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን ደብረብርሃን ከተማ እና በኦሮሚያ ብ/ክ/ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙ ሁለት ከተሞች ማለትም በሸናና በአሌልቱ ወረዳዎች በሚገኙ ቀበሌዎች የሚተገበር ነው።

ፕሮጀክቱ፣ እንደቀዳሚው ፕሮጀክት ሁሉ፣ የ18 ወራት የቆይታ ጊዜ የሚኖረው ሲሆን፣ በመጀመሪያው የፕሮጀክቱ ክፍል የተከናወኑ ተግባራት የበለጠ መሰረት እንዲይዙና እንዲጎለብቱ በማድረግ ላይ በዋናነት ያተኩራል። ፕሮጀክቱ በተለይ ትኩረት ያደረገው፣ የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎና የውሳኔ ሰጪነትን ሚና የበለጠ ማዳበር እና ማስፋት ላይ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ የአካባቢው ህብረተሰብ በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ የተለያዩ የመብት ጥሰቶችን በተመለከተ እያደረገ ያለውን ተሳትፎ የበለጠ እንዲያጠናክር የማድረግ ዓላማም አለው። እንዲሁም፣ ዕታዊ ትንኮሳን በመከላከል በኩል በየአካባቢው ያሉ የሴቶች መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች ተሣትፎ የበለጠ እንዲጎለብት የማገዝ ተልእኮም ይኖረዋል። እነዚህንና መሰል ተግባራትን ያካተተው ይህ ፕሮጀክት እንዲተገበር የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል። ፕሮጀክቱን የተመለከቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችም ተሰጥተዋል።

**የአእምሮ ብስለታችንን ለመገምገም አስፈላጊ ጉዳዮች**

- እውነታን ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ፣
- ሌሎችን ማፍቀር፣ (ይህም ተቃራኒ ዕታን ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ፍጡራንን ባጠቃላይ መውደድ ማለት ነው።)
- የመሰረታዊ ፍላጎት ችግርን መፍታት፣
- የራስን ጠንካራና ደካማ ጎን ጠንቅቆ ማወቅ፣
- ችግርንና ፍርሃትን መቋቋም፣
- ለሰብዓዊ ፍጡራን እንክብካቤ ሲባል ሃላፊነትን መቀበል፣
- በውስጣዊ ደካማ ስሜት ግፊት አለመመራት፣ (ይህም ሲባል፣ ለራስ ጥቅምና ምኞት ሌላውን ሰው አለመበደል፣ አለመጫን፣ ወዘተ.ነው።)

“ዶክተር፣ ፕሮፌሰር ...” ተብሎ መጠራት ከፍታ የመሰለን መሳሳታችንን፣ ከ2400 ዓመት በፊት የአቴናው ፈላስፋ አፍላጦን፣ የሌላኛውን ፈላስፋ የሶቅራጥሰን ሃሳብ ወስዶ፣ “እኔ የማውቀው አለማወቄን ነው/ I know that I know nothing” ብሎ የተናገረውን እናስታውስ!!!!

ምንጭ፡የፍትህ መጽሄት እትም

# ዓረብ ቤት የሚባለው የመንደር ገበያ መለወጥ

ጠላት ድል ሆኖ የኢትዮጵያ ነጻነት ከተመለሰ በኋላ ፣ በአዲስ አበባና በየጠቅላይ ግዛቱ ባሉት ዋና ዋና ከተሞች ከየመን እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ዓረቦች፣ ኪወስኮች በብዛት እያቋቋሙ ለየሰፈሩ ነዋሪ ህዝብ የሸቀጣ ሸቀጥ ችርቻሮ ንግዳቸውን አስፋፍተው ይኖሩ ነበር። ኢትዮጵያውያኖቹም ይህን በየሰፈራቸው የተመሰረተውን ንግድ ቤት "የዓረብ ቤት" እያሉ በመጥራት፣ ለእለት ኑሮ የሚያስፈልጓቸውን ዘይትና ስኳር፣ ጨውና ቅመማ ቅመም፣ ሻይና ቡና፣ ክብሪትና ሻማ፣ የፋኖስና የኩራዝ ማብሪያ የሆነውን ነጭ ጋዝና ለምባ፣ ዕጣንና ብርጉድ፣...የመሳሰሉትን ስለሚገዙ፣ የዓረቦቹ ንግድ እጅግ እየተስፋፋ ሄደ።

ይህን የመሰለው የንግድ ሥራ፣ ኢትዮጵያኖቹን በገዛ አገራቸው እጅግ የሚጎዳቸው መሆኑን የተገነዘቡት አቶ መኮንን ሀብተወልድ፣ እሳቸው በሚመሩት በንግድ ሚኒስቴር ውስጥ ሰፊ ጥናት ተደርጎ፣ አንድ መፍትሄ እንዲገኝለት ልዩ ኮሚቴ አቋቋሙ። የአቶ መኮንን ሀብተወልድ ጭንቀትና ሥጋት፣ የውጭ ዜጎች የሆኑት ዓረቦች፣ የኢትዮጵያውያኖች ቀጥታ መብት የሆነውን የየመንደሩን የችርቻሮ ንግድ በሙሉ ይዘው ከበርቴ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ዓረቦቹ በሚኖሩባቸው ቀበሌዎች ወጣት ሴት ልጆችን በገንዘብ አየደለሉ አንደ ሚስት በመያዝ ብዙ ልጆችን ካስወለዱ በኋላ፣ በመጨረሻው ለወለዷቸው ልጆች አንዳች የመኖሪያ ገንዘብም ሆነ የመቋቋሚያ ንብረት ሳያዘጋጁላቸው፣ ያከማቹትን ጥሬ ገንዘብ ይዘው የንግዳቸውን ድርጅት ለወገናቸው አስተላልፈው ወደ አገራቸው መመለሳቸው ነው። እነዚህ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑት ከዓረቦቹ ራስ በራስ የተወለዱት ህፃናት፣ አባቶቻቸው ባደ ሜዳ ላይ ጥለዋቸው ሲሄዱ፣ በየተወለዱበት መፈር ሲንገላቱና ሲቸገሩ ማየት እጅግ የሚያሳዝን ነበር። እነዚህን የዓረቦች ልጆች ማን ያኑራቸው? ማንስ ያሳድጋቸው?.... እናቶቻቸውም በየመፈሩ እነዚህ የዓረብ ሚስቶች እየተባሉ፣ እንኳንስ ለትዳር የሚፈልጋቸው፣ ለመራተኛነትም የሚቀጥራቸው ማግኘት አልቻሉም።

የንግድ ሚኒስቴር ዋና ዋና ሃላፊዎችና የኢትዮጵያ ህዝብ ያገር ፍቅር ማህበር አባሎች የተገኙበት ኮሚቴ ጥናቱን አካሂዶ ባቀረበው ሀሳብ መሰረት የንግድ ሚኒስትሩ በዚህ ከኮሚቴው በቀረበላቸው ሀሳብ ውስጥ፣ ወደፊት በየመፈሩ ለሚካሄደው የችርቻሮ ንግድ ሥራ ለውጭ አገር ዜጎች መከልከሉን አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ነው ብለው ቢያምኑበትም፣ የችግሩ የመጨረሻው መፍትሄ አለመሆኑን በማየት፣ ዓረቦቹ የያዙትን ሥራ ኢትዮጵያውያኖች ወዲያውኑ እንዲረከቡ ለማድረግ ዘዴው ምን እንደሆነ ኮሚቴው ጥናቱን እንዲቀጥል ጠየቁ።

በዚህ ውሳኔ መሰረት፣ የንግድ ሚኒስቴርና የአገር ፍቅር ማህበር አባሎች ተሰብስበው ጥናታቸውን በሚያካሄዱበት ጊዜ፣ ለዚህ ኮሚቴ ቃለጉባኤ ያዥና ላይዘን ኦፊሴር ሆኖ እንዲሠራ መኮንን ሀብተወልድ የመረጡት "ሩጋ አሻሜ" የተባለ ዕድሜው ሠላሳኛውን ዓመት ያልሞላ ወጣት፣ አንድ ሀሳብ ተገለጠለት። ይኸውም፣ ለወጣቱ ሩጋ (በኋላ የፊታውራሪነት ማዕረግ አግኝተዋል) የታየው፣ በዚህ የመፈር ችርቻሮ ንግድ ዓረቦቹን ተቋቁመው የተያዙትን ቦታዎች ማስለቀቅ የሚችሉት የትውልድ አገሬ ተወላጆች "ጉራጌዎች " ብቻ ናቸው የሚል ነበር።

መኮንን ሀብተወልድ ወጣቱ ሩጋ ባቀረበላቸው ሀሳብ በጣም ተማረኩ። በማግስቱም በአገር ፍቅር ማህበር ጽህፈት ቤታቸው ኮሚቴውን ሰብስበው፣ የሩጋ አሻሜን ስም ሳያነሱ፣ ከአንድ ትጉህ ሠራተኛዬ የቀረበልኝ በሚል መነሻ ሀሳቡን ተንትነው ለአባሎቹ ገለፁ።

በመጨረሻም፣ በወጣቱ ሩጋ አሻሜና በጓደኞቹ ጥረት ለመጀመሪያ ጊዜ ተመርጠው የቀረቡት ዐርባዎቹ የጉራጌ ነጋዴዎች፣ የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ ተቀብለው በአዲስ አበባ ከተማ ሥራቸውን በአስቸኳይ እንዲጀምሩና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚያሳዩት ውጤት ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት የኮሚቴው አባሎች በሙሉ ከስምምነት ላይ ደረሱ። እነዚህም ዐርባዎቹ ወጣት ነጋዴዎች፣ በየሰፈሩ በሚገኘው ዓረብ ቤት አጠገብ ሱቅ እያቋቋሙ ንግዳቸውን ለመጀመር ወደፊት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሚያገኙት ትርፍ የሚከፍሉት ለእያንዳንዳቸው ሰባት መቶ የኢትዮጵያ ብር መንግስት እንዲያበድራቸው ኮሚቴው የተስማማበትን፣ መኮንን ሀብተወልድ ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበው አስፈቀዱ።

እንደታሰበውም፣ ጉራጌዎቹ ነጋዴዎች በየዓረቡ መደብር አጠገብ ሱቆቻቸውን እየተከሉ፣ ንግዳቸውን ሲጀምሩ፣ የሠፈርተኛው ህዝብ መልካም ትብብር ስላልተለያቸው፣ ያደረባቸው ትጋትና የጋለ ስሜት እጅግ የተለየ ሆኖ ይታይ ነበር። አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥም፣ ከዐርባዎቹ ነጋዴዎች መካከል ሠላሳ ሦስቱ በዓረቦቹ ተይዘ የነበረውን ንግድ በሙሉ ቀልብሰው ስለወሰዱት፣ የመኖቹ የነበራቸውን ሱቅ እያፈረሱ ከሠፈሩ መጥፋት ግዴታ ሆነባቸው።

ምንጭ፡- ዘውዴ ረታ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት፣ገፅ 618

## ከአለቃ ገብረሃና ቀልዶች

በሀገራችን እንደተለመደው ድግስ ካለ ቄሱም፣ አዝማሪውም፣ ሼሁም ሁሉም እንደሃይማኖቱ ይጠራል። ስለዚህ፣ የአለቃ ግዳጅ አንዱ ድግስ መሄድ ነው። ሴትየዋ ያው እንደነገሩ አሸር ባሸር የሆነ ድግስ ብጤ አድርጋ ኖሮ አለቃ ወጡም ቅጥንጥን፣ ጠላውም ውሃ ውሃ ብሎባቸው ኖሯል። ደጋሿ መጥታ አለቃ "ይብሉ እንጂ ትላለች!"። አለቃም "የመጣንበትን ቢሻን እንበላለን፤ ቢሻን እንጠጣለን!" ብለው የልባቸውን ተናገሩ።




የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ የቀድሞ እና የ4ኛው ዙር ተመራቂ ተማሪዎች




የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ የ3ኛው ዙር የባህርዳር ተመራቂ ተማሪዎች ከፋዌ ኢትዮጵያ የጽ/ቤት ሃላፊ ጋር

# የፋዌ ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተሮች የ2013 ዓ.ም. የሥራ እንቅስቃሴ

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከምስረታው ጊዜ አንስቶ ለበርካታ ዓመታት በውጤታማነት እንዲዘልቅ በየክልሉ የተቋቋሙ የፋዌ ንዑስ ቻፕተሮች ሚና ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። የእነዚህ ንዑስ ቻፕተሮች በየክልሉ መቋቋም፣ ከሴት ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ጋር በተያያዘ በየክልሎቹ የሚስተዋሉ ችግሮችን መቅረፍ የሚያስችሉ ተግባራትን የየክልሎቹን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲከናወኑ አድል ሰጥቷል፡ ፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ፋዌ ኢትዮጵያ የተደራጀበትን ዓላማ በሃገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ማስረፅ የሚቻልበትን አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል፤ የድርጅቱም የድጋፍ መሰረት እንዲሰፋ አስተዋፅኦ አድርጓል። እነዚህ ንዑስ ቻፕተሮች፣ በ2013 በጀት ዓመት አቅዳቸውን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ተግባራትን አከናውነዋል። በመሆኑም፣ የተወሰኑ የክልል ፋዌ ንዑስ ቻፕተሮችን የሥራ እንቅስቃሴ የተመለከተ ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ፋዌ ኢትዮጵያ ሐረር ንዑስ ቻፕተር

በሐረር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ከተማ ሐረር የተቋቋመው ይህ ንዑስ ቻፕተር፣ በ2013 ዓ.ም. የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል። በዚህም መሰረት፡-

- ✓በሴቶች ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱና በክልሉ ከሚገኙ ማኅበራት ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ ሴት ተማሪዎችን የማበረታታት ሥራ ተሠርቷል።
- ✓ ሴት ተማሪዎች በሚያጋጥሟቸው የተለያዩ ችግሮች የተነሳ ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ፣ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ የትምህርት መሣሪያዎችንና የግል

ንፅህና መጠበቂያዎችን (ሞደስ) በመስጠት፣ በትምህርታቸው ላይ የሚደርሱ ተፅእኖዎችን የመቅረፍ ሥራ መሥራት ተችሏል። ይህም፣ ተማሪዎቹ ትምህርታቸው ላይ የበለጠ ትኩረት እንዲያደርጉና የትምህርት ውጤታቸውም ከፍ እንዲል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ያጋጠሙ ችግሮች፡-
በክልሉ ፋዌ ቻፕተር የሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ላይ በችግርነት የሚጠቀሱ በርካታ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም፣ የሚከተሉት ግን በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህም፣

✓ኮቪድ-19፣ በትምህርት ቤቶች የትምህርት አሰጣጥ ላይ ባስከተከለው ተፅእኖ የተነሣ፣ የትምህርት አሰጣጡ በፈረቃ እንዲሆን መደረጉ፣ የቻፕተሩ ጽ/ቤት በሚያከናወነው ሥራ ላይ ተፅእኖ ማድረጉ፣

✓እንደማንኛውም የሃገራችን ክልል፣ በሐረርም ኢኮኖሚያዊም ሆነ ትምህርት ነክ ድጋፎችን የሚሹ በርካታ ሴት ተማሪዎች የሚገኙ ቢሆንም፣ ባለው ኢኮኖሚያዊ አቅም ውስንነት የተነሣ እንደ ቻፕተር ጽ/ቤቱ ፍላጎት መንቀሳቀስና እነዚህን ሴት ተማሪዎች መደገፍ አለመቻሉ፣ የሚሉት ናቸው።

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋዌ ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተር ዓመታዊ እንቅስቃሴ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋዌ ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተር፣ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የፋዌን ዓላማ መሰረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል፡ ፡ ንዑስ ቻፕተሩ እንቅስቃሴውን ከሚያደርግባቸው ትምህርት ቤቶች መካከል አንዱ፣ የደራርቱ ቱሉ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቱ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ተማሪዎችን በተለይም ሴት ተማሪዎችን በመደገፍና በማበረታታት በክፍለ ከተማው ብሎም በከተማ ደረጃ ከሚጠቀሱ ትምህርት ቤቶች መካከል ግምባር ቀደም ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋዌ ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተር ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ፣ በአብዛኛው ትኩረት ያደረገው በዚህ ትምህርት ቤት በተከናወኑ ዐበይት ተግባራት ላይ ነው። ተግባራቱ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

✓የትምህርት ቤቱን ሁሉንም ማህበረሰብ፣ የማህበራዊ አገልግሎት ተሳታፊና አባል እንዲሆን እና በአባልነትም በዓመት ሃያ ብር እንዲያዋጣ በማድረግ፣ በኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተነሳ ትምህርታቸውን በወጉ መከታተል የማይችሉ ተማሪዎችን በጋራ መደገፍ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትና ተማሪዎቹንም መታደግ ተችሏል።

✓ሴት ተማሪዎችን የሥርዓተ ፆታ ክበብ አባል እንዲሆኑ በማድረግ፣ ሥነ ተዋልዶንና ኤችአይቪን አስመልክቶ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል።

✓ሴት ተማሪዎች፣ በትምህርት ገበታ ላይ በድንገት በሚከሰት የወር አበባ የተነሳ ጭንቀት ላይ እንዳይወድቁና ስጋትም እንዳይገባቸው ለማድረግ፣ በየአለቱ የንፅህና መጠበቂያ ሞደስ አቅርቦት እንዲመቻች ማድረግ ተችሏል። በዚህ ረገድ፣ የትምህርት ቤቱ የቀይ መስቀል ከበብና በትምህርት ቤቱ አካባቢ የሚገኘው የኤቴል የእናቶችና ህፃናት ክሊኒክ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር።

✓የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው 23 የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች፣ እስከ 2012 ዓ.ም. አንደኛ ሴሚስተር ድረስ በጀግናዋ አትሌት ኮለኔል ደራርቱ ቱሉ አማካይነት በሚደረግላቸው የገንዘብ ድጋፍ፣ በተለያዩ የግልና የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተዋል።

✓በ2013 ዓ.ም. በትምህርት ቤቱ በመማር ላይ የሚገኙና የወለጆቻቸው የኢኮኖሚ አቅም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘታቸው የተረጋገጠ 4 ወንዶችና 13 ሴት ተማሪዎች፣ በድምሩ 17 ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በሚሰበሰብ መዋጮ በትምህርት ቤቱ የምሳ ምገባ ተጠቃሚ ሊሆኑ ችለዋል።

✓የደራርቱ ቱሉ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆነችና በሰው ቤት በሠራተኛነት እየሠራች በመማር ላይ የነበረች ተማሪ፣ በገጠማት ከፍተኛ የሥራ ጫና የተነሣ ትምህርቷን በአግባቡ መከታተል ባለማቻሏ፣ የትምህርት ቤቱ የማህበራዊ አገልግሎት አባል ለሆኑ አንዲት በጎ ፈቃደኛ ሴት በአደራ በሞግዚትነት እንድትሰጥ በማድረግ፣ ተማሪዋ ትምህርቷን ባግባቡ እንድትከታተል ተደርጓል።

ያጋጠሙ ችግሮች

✓ከዚህ በፊት ተማሪዎችን በመደገፍ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውኑ የነበሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች ድጋፍ መቋረጥ፣ ከዚህ የተነሣም በሚደረግላቸው የገንዘብ ድጋፍ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ችግር ላይ የሚገኙ መሆኑ፣

✓በኮቪድ-19 የተነሳ፣ በአንድ ክፍል ውስጥ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ወደ ሁለት ክፍል እንዲበተኑ መደረጉ፣ በክበባት ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ተፅእኖ ማሳደሩ፣ የንዑስ ቻፕተሩን እንቅስቃሴ አስቸጋሪ ማድረጉ፣

✓በፋዌ ኢትዮጵያ ጽቤት በኩል ለቻፕተሩ እንቅስቃሴ የሚመደበው በጀት፣ ትምህርት ቤቱ ካለው የተማሪ ቁጥርና ማሟላት ከሚጠበቅበት ግብዓት አንፃር በሚፈለገው መጠን ተገቢውን የሥራ እንቅስቃሴ እንዳያደርግ የገደበው መሆኑ፣

## የሃዋሳ ፋዌ ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተር

የሃዋሳ ፋዌ ቻፕተር ቀድሞ በደቡብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ንዑስ ቻፕተር በመሆን የፋዌን ተግባራት ሲያከናወን የቆየ ሲሆን፣ አሁን ግን ራሱን ችሎ የተዋቀረ ንዑስ ቻፕተር ነው። የንዑስ ቻፕተር ጽ/ቤት፣ ቀድሞ እንደደቡብ ክልላዊ መንግስት በሃዋሳ ከተማ በፋዌ ኢትዮጵያ ፕሮግራም መሰረት ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን መቻሉን የተገነዘበው የደቡብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ፣ በ2012 ዓ.ም. ባካሄደው ዓመታዊ የትምህርት ጉባኤ ላይ የእውቅና ሰርቴፊኬት የሰጠው መሆኑ ይታወሳል። ንዑስ ቻፕተሩ፣ በ2013 በጀት ዓመት ያከናወናቸው ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

✓የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች ተጠቃሚነት 100% ተሳክቷል።

✓የሁለተኛው ዙር የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርስቲ እንዲገቡ የነበረውን እቅድ ማሳካት ተችሏል።

✓የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ተማሪዎችን ሁለንተናዊ እርካታ (ከትምህርት፣ ከግብዓት አንፃር) 100% ማሳካት ተችሏል።

✓የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን ቤት ለቤት የመጎብኘት ተግባር ተከናውኗል።

✓የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች፣ በየሚማሩበት ትምህርት ቤቶች በትምህርት አሰጣጥ፣ በቱቶሪያል አተገባበር እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ስለሚኖራቸው ጤናማ መስተጋብር በተመለከተ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ውይይቶች ተካሂደዋል።

✓ የተለያዩ ስልጠናዎች ሲሰጡ በመከታተል፣ በማጠቃለያ ፕሮግራሞቻቸውም ላይ በመገኘት፣ በየስልጠናዎቹ ሂደት የነፃ ትምህርት

አድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች ያገኙትን ግብዓትና ጥቅም በማሰባሰብ ለቀጣይ እንቅስቃሴ ግብዓት እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ ማደራጀት ተችሏል።

✓የመጨረሻው ዙር የነፃ ትምህርት አድል ተጠቃሚ ተማሪዎችን መረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት፣ ከዋናው ፋዌ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ለሚመጣው ቡድን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ከመቻሉ በተጨማሪ፣ አዲስ ተጠቃሚዎችን በመመልመል ሂደት ውስጥም በመሳተፍ አጠቃላይ የቻፕተር ጽ/ቤቱ እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል ሥራ ተሰርቷል።

✓ለሴት ተማሪዎች የትምህርት፣ የንፅህና መጠበቂያ፣ ለቤት ውስጥ አገልግሎታቸው በሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶች ስርጭት ወቅት የክትትልና የድጋፍ ሥራ ተከናውኗል።

✓በየወቅቱ በሚደረጉ የፕሮጀክት አፈፃፀም ግምገማዎች ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ተችሏል።

✓በተለያዩ ጊዜያት ከዋናው ጽ/ቤት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠትና አስፈላጊ ሁኔታዎችንም የማመቻቸት ሥራ ተግባራዊ ተደርጓል።

✓በኮቪድ-19 ወረርሽን ምክንያት ትምህርት በተቋረጠበት ሰዓት፣ ለማስተርክርድ ፋውንዴሽን ስክላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች በአንላይን የሚሰጡ ትምህርቶችን ሀንድ አውቶች፣ የወርክሾፕ ጥያቄዎችን በቅርበት ማግኘት የማይችሉ ተማሪዎችን የተመለከተ መረጃ፣ ከትምህርት ቤቶቻቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በየወቅቱ በመሰብሰብ፣ ተማሪዎቹ የተጠቀሱት ችግሮች ሰለባ እንዳይሆኑ ከፍተኛ ጥረት በማድረግና ተገቢውንም ድጋፍ በመስጠት ትምህርታቸውን ባግባቡ የሚከታተሉበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ተችሏል።

በበጀት ዓመቱ ታቅደው ያልተከናወኑ ተግባራት፡-

✓ለጠቅላላ የንዑስ ቻፕተሩ አባላት አጭር የግንዛቤ ማስፊያ (Re-freshment) መድረክ የማመቻቸትና ስልጠና የመስጠት አቅድ አለመሳካቱ፣

✓የነፃ ትምህርት አድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን የተመለከተ የፋዌ ንዑስ ቻፕተሩን ጠቅላላ የአባላት የጋራ የውይይት መድረክ ለማዘጋጀት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ በነበረው ወቅታዊ ችግር የተነሳ ሊተገበር አለመቻሉ፣

✓የነፃ ትምህርት አድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን የየሴሚስተሩን ውጤት መነሻ በማድረግ በግል ደረጃ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ አሁንም በኮቪድ-19 የተነሳ ድጋፍና ክትትል የማድረጉ አቅድ ሊተገበር አለመቻሉ፣

በመጨረሻም፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ከተመሰረተበት ዓላማ አንፃር የመንግስትን ፖሊሲ በመደገፍ የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ በማሳካት በትምህርታቸው ብቁና ውጤታማ የሆኑ ሴት ተማሪዎችን ቁጥር ከማበራከት ባሻገር፣ ዛሬ ላይ በፕሮግራሞቹ ውስጥ ወንድ ተማሪዎችንም ተደራሽ ያደረጉ ተግባራትንም በማከናወን ላይ ይገኛል። ይሁን እንጂ፣ ይህ የያዝነው በጀት ዓመት የነፃ ትምህርት አድል ምልመላ መጨረሻ ዙር ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ፣ በፈጣን የአድገት እንቅስቃሴ ላይ ከምትገኘው ሃዋሳ ከተማ አንፃርና ከከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያየ ምክንያት ወደከተማዋ የሚፈልሰው ሰው ቁጥር በጣም ከፍተኛ በመሆን ላይ ነው። ይህም ሁኔታ፣ በከተማዋ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከአቅማቸው በላይ በርካታ ተማሪዎችን እንዲያስተናግዱ እያስገደደ ይገኛል። በተለይም፣ በሴት ተማሪዎች ቁጥር ላይ የታየው ለውጥ ከፍተኛ መሆኑን፣ በ2012 ዓ.ም. ትምህርት ገበታ ላይ ከነበሩ ተማሪዎች መካከል የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶቹ ይልቅ ከፍተኛ መሆኑን ከሚጠቁሙ መረጃዎች መረዳት ይቻላል። እንደሚታወቀው፣ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በሌሎች በርካታ ጉዳዮች የተነሳ ወላጆቻቸውን ካጡትና ለችግር ከተጋለጡት በርካታ ቁጥር ካላቸው ተማሪዎች መካከል አብዛኛዎቹ ሴት ተማሪዎች መሆናቸውን መገመት አያዳግትም። ይህም በመሆኑም፣ በንዑስ ቻፕተሩ ጽ/ቤት የሚከናወኑ ተግባራትን በተጠናከረ ሁኔታ ማስኬድ እጅግ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ፣ ጽ/ቤቱን በጽ/ቤት ደረጃ ከማጠናከር ጀምሮ ሌሎች የተለያዩ ተግባራትን አጠናክሮ ማስቀጠል እጅግ ጠቃሚ ነው።

## ፋዌ ኢትዮጵያ ኦሮሚያ ንዑስ ቻፕተር

በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኘው የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር፣ በአዳማ ከተማ በ8 መለስተኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንቅስቃሴ የሚያደርግ መሆኑ ይታወቃል። የንዑስ ቻፕተሩ ጽ/ቤት፣ እነዚህን ትምህርት ቤቶች ባማከለ መልኩ በ2013 ዓ.ም. በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ቢሆንም፣ በዓለም አቀፍና በሃገር አቀፍ ደረጃ ባጋጠመው የኮቪድ-19 በሽታ የተነሳ ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉና ለተወሰነ ጊዜም የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲቋረጥ መደረጉ፣ እቅዱን በሚገባው መልኩ መፈፀም እንዳይችል እንቅፋት መሆኑ አልቀረም። ይሁን እንጂ፣ በበጀት ዓመቱ የትምህርት ሂደቱ የበሽታውን ስርጭት ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ በፈረቃ እንዲቀጥል የተደረገበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የንዑስ ቻፕተሩ ጽ/ቤት የሚንቀሳቀስባቸውን ትምህርት ቤቶች መሰረት በማድረግ፣ ለተማሪዎች በአጠቃላይ በተለይም ለሴት ተማሪዎች በተለያየ መልኩ ለበሽታው እንዳይጋለጡ በተለያየ መልኩ እገዛ ያደረገበትን እንቅስቃሴ ለማከናወን ጥረት አድርጓል። የንዑስ ቻፕተሩ ጽ/ቤት፣ በኮቪድ-19 ውስጥ ሆኖ በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሴት ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ኮቪድ-19ን በተመለከተ ርቀታቸውን እንዲጠብቁ፣ ሁልጊዜ የእጃቸውን ንፅህና እንዲጠብቁ፣ ሳኒታይዘር እንዲጠቀሙና ማስክ በመጠቀም ረገድ እንዳይዘናጉ ያልተቋረጠ የግንዛቤ ሥራ ተሠርቷል።

በተቻለ መጠን የንፅህና መጠበቂያ ሞዴስ፣ ሳኒታይዘርና ማስክ የመስጠት ሥራ ተከናውኗል።

ሴት ተማሪዎችን ለማብቃት የሚያስችል የምክር አገልግሎት እና ትምህርታቸውንም በብቃት እንዲከታተሉ እና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችሏቸው የተለያዩ እገዛዎች ተደርገዋል።

የኮቪድ-19 በሽታ በቤተሰቦቻቸው ላይ ባደረሰው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የተነሳ ከትምህርት ገበታቸው ላይ ሊፈናቀሉ የሚችሉ ተማሪዎች፣ ከትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳይፈናቀሉ የሚያደርግ እገዛ ተደርጓል፤ የማበረታታትና የማነቃቃት ሥራም ተሠርቷል።

በአጠቃላይ፣ ኮቪድ-19 እንደሃገር የነበረው ተፅእኖና እያስከተለው ያለው ችግር፣ ፋዌ ኦሮሚያ በትምህርት ቤት ላይና በሴት ተማሪዎች ላይ ሊሠራ ያሰበውን እቅድና እንቅስቃሴ በተሟላ መልኩ እንዳይተገብር አግዶታል። ኮቪድ-19፣ እንደሃገር ተፅእኖው እንደመቀጠሉ፣ በሴት ተማሪዎች ላይ የሚያስከትለው ዘርፈብዙ ችግርም እንዲሁ አሁንም ቀጣይነት እንደሚኖረው በመገንዘብ፣ የፋዌ

ኢትዮጵያ ኦሮሚያ ንዑስ ቻፕተርም ሆነ ሌሎች በሴት ተማሪዎች ላይ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አካላት፣ አቅም በፈቀደ መጠን የኮቪድ-19 ዘርፈ ብዙ ተፅእኖዎችን ታሳቢ በማድረግ ሊደረጉ የሚገቡ እገዛዎችን በመለየት እንቅስቃሴዎቻችንን በትብብር አጠናክረን መቀጠል እንዳለብን የንዑስ ቻፕተሩ ጽ/ቤት ያሳስባል።

## የፋዌ ኢትዮጵያ የቀድሞ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚዎች ዓመታዊ ጉባኤ እና የ2013 ዓ.ም. ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች የምረቃ ሥነስርዓት



ዶ/ር ቶላ በሪሶ፣ የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ ሃላፊ፣ ተማሪዎችን ሲሸልሙ

የቀድሞ የፋዌ ኢትዮጵያ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ዓመታዊ ጉባኤ እና የ2013 ዓ.ም. የፋዌ ኢትዮጵያ ማስተርካርድ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ምረቃ ሥነስርዓቶች ታህሣሥ 1 እና 2 2014 ዓ.ም. ለአራተኛ ጊዜ በቢሾፍቱ ከተማ ተካሄዱ። ሁለቱም ሁነቶች በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄዱ፣ በሚመለከታቸው አካላት ተገቢዎቹ ቅድመ ዝግጅቶች ቀደም ብለው ተካሂደዋል። ቢሾፍቱ ከተማ በሚገኘው የኢትዮጵያ ሥራአመራር ኢንስቲትዩት የስልጠና ማእከል የስብሰባ አዳራሽ በተካሄዱት በእነዚህ ሥነስርዓቶች፣ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ ዋና ተዋናዮች የሆኑት የማስተርካርድ ፋውንዴሽን እና የፋዌ ኢትዮጵያ የጽ/ቤት ሃላፊዎችና ሠራተኞች፣ የተማሪዎች ተወላጆችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል። በዘንድሮው የቀድሞ የፋዌ ኢትዮጵያ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ማህበር ዓመታዊ ጉባኤ ላይ፣ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር እና የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙን ዓላማና አፈፃፀም፣ እንዲሁም በፕሮግራሙ የተመዘገቡ ውጤቶችን የተመለከተ ማብራሪያ በፋዌ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር በወ/ሮ ሮማን ደገፋ እና በጽ/ቤቱ የፕሮግራም አስተባበሪ በሆኑት በአቶ ፍቅሩ አማካይነት ማብራሪያና ገለፃ ተሰጥቷል። እንዲሁም፣ የቀድሞ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ማህበርን ዓመታዊ እንቅስቃሴን የተመለከተ ገለፃና በቀጣይም የማስተርካርድ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም በሚተገበርባቸው ክልሎች በማህበሩ አማካይነት እንዲከናወኑ የታቀዱ ዝርዝር ተግባራትን ያካተተ ረቂቅ አቅድ በማህበሩ ሥራአስፈፃሚ አማካይነት ቀርበዋል፤ ውይይትም ተካሂዶባቸዋል፣ ፡ በዚሁ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ፣ የ2013 ዓ.ም. ተጠቃሚ የሆኑ 136 ተማሪዎች የዚሁ ጉባኤ ተሳታፊ ከመሆናቸውም በላይ፣ በማህበሩ ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉም የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ የሚተገበርባቸውን ክልሎችን የወከሉ ሁለት ሁለት አባላትን ለማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ በአባልነት መርጠዋል።

የዘንድሮ የ2013 ዓ.ም. የፋዌ ኢትዮጵያ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ተመራቂ ተማሪዎች ዓመታዊ የምረቃ ሥነስርዓትም እንዲሁ ታህሣሥ 2 ቀን 2014 ዓ.ም. ተካሂዷል። በእለቱ የምረቃ ሥነስርዓት ላይ፣ ዶ/ር ቶላ በሪሶ፣ የኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ ሃላፊ፣ ወ/ሮ የሻረግ ነጋሽ በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ፆታ ዳሬክቶሬት ዋና ዳይሬክተር፣ ወ/ሮ አልማዝ ወልደተንሣይ የፋዌ ኢትዮጵያ የቦርድ ሰብሳቢ፣ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ የሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች የሚገኙባቸው ወረዳዎች የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ጽ/ቤቶች ተወካዮች፣ የየትምህርት ቤቶቹ ዳይሬክተሮች፣ የመምህራን ሜንቶሮች እና ወላጆችና የፋዌ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ሠራተኞች ተገኝተዋል። በዚሁ ምረቃ ላይ በእንግድነት የተገኙት ዶ/ር ቶላ በሪሶ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልደተንሣይ ለተመራቂ ተማሪዎች የመልካም ምኞትና የእንኳን ለዚህ በቃችሁ ንግግር አድርገዋል። የተመራቂ ተማሪዎች ወላጆችም፣ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ በልጆቻቸው የትምህርት ተሳትፎ ውስጥ የነበረውን ዓይነተኛ አስተዋፅኦ በተመለከተ የበኩላቸውን ምስክርነት ገልፀዋል፤ ተመራቂ ተማሪዎችም እንዲሁ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ከታቀፉ አንስቶ በትምህርታቸው ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንደቻሉ ከፍተኛ እገዛ እንደነበረው አብራርተዋል። በመጨረሻም፣ ለተመራቂ ተማሪዎች በሙሉ የሠርተፊኬት እና በትምህርታቸውም ከፍተኛ ውጤት ለስመዘገቡ ተመራቂ ተማሪዎች ሽልማት የመስጠት ሥነስርዓት ተካሂዶ የአለቱ ፕሮግራም ተጠናቋል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ ቢሾፍቱ የተካሄደውን ይህን የተማሪዎች የምረቃ ሥነስርዓት ተከትሎ፣ የፋዌ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ ለሆኑና ባህርዳር ከተማ ውስጥ ለሚገኙ 46 ተማሪዎች የምረቃ ሥነስርዓት ተካሂዷል። የምረቃ ሥነስርዓቱ ታህሣሥ 14 ቀን 2014 ዓ.ም. ባህርዳር ከተማ ውስጥ በሚገኘው አለይቭ ሆቴል ተካሂዷል። በምረቃው ሥነስርዓት ላይ የተለያዩ ጥሪ የተደረገላቸው የአማራ ክልል የትምህርት እና የሴቶች፣ የህፃናትና ወጣቶች ቢሮዎች ተወካዮች፣ እንዲሁም የፋዌ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም የሚተገበርባቸው ትምህርት ቤቶች የሥራ ሃላፊዎች እና መምህራን፣ የተመራቂ ተማሪዎች ቤተሰቦች እና የፋዌ ኢትዮጵያ የጽቤት ሠራተኞች ተገኝተዋል። በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ለስመዘገቡ ስድስት ተማሪዎችም (ሁሉም ሴቶች ናቸው) የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቷል።





የማስተርካርድ ስኮላርሽፕ የ4ኛው ዙር ተጠቃሚ ተማሪዎች የምረቃ ሥነሰርዓት እና
የቀድሞ ተማሪዎች ስብሰባ ሂደት በከፊል (ቢሾፍቱ)

## ከጠቢባን ምክር

❖ አጭር ርቀትን ብቻህን ብትጓዝ ይመረጣል። ረጅም ርቀትን ግን ከሰው ጋር ብትጓዝ ይሻላል። ከሞኝ ሰው ጋር ደግም አንድ ኢንችም አብረኸው አትጓዝ። ቀንህን ያደፈረስብሃል። ጉዞህ ደስታ ቢስ እንዲሆን ከፈለክ ከሞኝ ጋር ተጓዝ!!

❖ ለመኖር ብላ እንጂ፣ ለመብላት ብቻ አትኑር!!!

## ከዘነበ ኢትዮጵያዊ መጽሃፈ ሥጋዊ መንፈሳዊ፣1857

➢ ድንጋይና ጭቃ ቢቀጣጠሉ ታላቅ ቤት ረጅም ቅጥር ይሆናሉ። እናንተም መሬታውያን ሰዎች እንደዚህ ብትረዳዱ ጥበባችሁና ሃይላችሁ ከሰማይ በደረሰ።

➢ በርበሬ ላዩን ቀይ ሆኖ ይታያል፤ ምነው ቢሉ በብልሃት ገብቶ ሊለበልብ ፡ ፡ ክፉ ሰውም ቀስ ብሎ ገብቶ ኋላ ነገሩን ያመጣል።

➢ ከገንዘብ መልካም ማነው፤ወርቅ። ነገርንና ጥልን የሚያስቀር ማነው፡ ዕርቅ። ኑዋሪስ ማነው፡ ዓዲቅ ነው፡ ሣቅስ ምንድን ነው፡ የደስታ ማለፊያ ነው፡ እልልታ ምንድን ነው፡ የደስታ መክፈያ አዋጅ ነው።

➢ ቀለም በቀንድ ሳለ ዲዳ ነው፡ ፡ በተግፈ ጊዜ ግን መላሰኛ ነው። ቀለም በቀንድ ሳለ ጭምት ነው። በተግፈ ጊዜ ግን እንደሰከረ ነው። ሁሉንም ይለፈልፋል።

➢ የምሥራች ከሩቅ አገር በመጣ ጊዜ የሰው ልብ በደስታ ባህር ይሰጥማል፡ ፡ እርጎን ከፍተው ቢተዉት ዝንብና ድመት ይጫወትበታል። አገርንም አቅንቶ ሰው ካለሳቀመጡበት ተመልሶ ዱር ይሆናል።

# የፋዌ ኢትዮጵያ ስኮላርሽፕ ተጠቃሚ ተማሪ ምስክርነት

ፋዌ ኢትዮጵያ በትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው ባሉባቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የተነሳ ትምህርታቸውን ባማባቡ መከታተልና በትምህርታቸውም የመዘለቅ አዳጋ የተጋረጠባቸውን ሴት ተማሪዎችን የተለያዩ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሞችን በመዘርጋት ሲደግፍ ቆይቷል፤ በመደገፉም ላይ ይገኛል:: በፋዌ ስኮላርሽፕ ፕሮግራሞች በሚደረጉላቸው የተለያዩ ድጋፎች እየታገዙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚገባ ያጠናቀቁ፣ በርካታ ሴት አህቶታችን ተጠቃሽ ናቸው። ከእነዚህ ሴት አህቶቻችን መካከል አንዷ ተማሪ ዳግማዊት ፍቃዱ ናት። ዳግማዊት ፍቃዱ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን በሚገባ በማጠናቀቅ የዩንቨርስቲ ትምህርት መግቢያ ፈተናና በመውሰድ ውጤቷን በመጠባበቅ ላይ የምትገኝ ስትሆን፣ የፋዌ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ ፕሮግራምን በተመለከተ ያላትን አስተያየት እንድትሰጠን ቃለመጠይቅ አድርገንላታል። የቃለመጠይቁ ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ትማር፡-** ራስሽን ብታስተዋውቂን?

**ዳግማዊት ፍቃዱ፡-** ስሜ ዳግማዊት ፍቃዱ ይባላል። የተወለድኩት ሐምሌ 1 ቀን 1994 ዓ.ም. ሲሆን፣ የተወለድኩት ሀዋሳ ከተማ በተለምዶ ኮረም ሰፈር በመባል በሚታወቀው አካባቢ ነው። ለቤተሰቤ ሁለተኛ ልጅ ነኝ።

የቤተሰብ ሁኔታን በተመለከተ፣ አባት እና እናቴን ጨምሮ በአጠቃላይ የቤታችን አባላት ብዛት አምስት ነው። ታላቅ እና ታናሽ ሁለት አህቶች አሉኝ። ታላቅ አህቴ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማኔጅመንት የሶስተኛ ዓመት ተማሪ ናት። ታናሼ ገና ትምህርት አልገባችም::

አባቴ አቶ ፍቃዱ ተሾመ የቴሌ ሰራተኛ ሲሆን፣ እናቴ ወ/ሮ መስከረም ጌታቸው ሀዋሳ ፖሊስ መምሪያ ውስጥ ትሰራለች። የትምህርት ሁኔታዬን በተመለከተ፣ ከነርሰሪ እስከ ኬጂ ድረስ ሃዋሳ በብራይት ፊውቸር ትምህርት ቤተ የተማርኩ ሲሆን፣ አንደኛ ክፍልን ስለሴ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከሁለተኛ እስከ ስምንተኛ ያሉ ክፍሎችን ደግሞ ኢትዮጵያ ትቅደም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትያለሁ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ደግሞ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ በማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ባዘጋጀው የስኮላርሽፕ ፕሮግራም እድል ተጠቃሚ በነበርኩበት ወቅት ቢኢንቢ በተሰኘ ትምህርት ቤት በመማር አጠናቅቄአለሁ። በቅርቡ፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ ጥቅምት መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የ2013 ዓ.ም. የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና ወስጄ ውጤት በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ።

**ትማር፡ -** የፋዊ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆንሽ ይታወቃል፡ ፡ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ እንዴት ልትሆኚ ቻልሽ?

**ዳግማዊት ፍቃዱ፡ -** የፋዊ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆንኩት፣ የኢትዮጵያ ትቅደም መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ በመጣው አድል ልታቀፍ በመቻሌ ነው። ይህን አድል ያኘሁት፣ በዋናነት በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት ላላቸው ተማሪዎች በተሰጠው እድል መሰረት ባጋኘሁት ውጤት ተወዳድሬ ነው። በመሆኑም፣ ውድድሩ ሲካሄድ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ በሰባተኛ እና በስምንተኛ ክፍሎች የተመዘገበ ውጤት እና በክልል ደረጃ በሚሰጠው ክልላዊ የስምንተኛ ክፍል ፈተና የተገኘ ውጤትም በመመልመያ ጥቅም ላይ እንደዋሉና እነዚህንም መስፍርቶች እንዳሟላሁ አስታውሳለሁ። ከውጤቴ በተጨማሪ፣ በውድድሩ ወቅት በተለያዩ ክበቦች እና በተለያዩ ትምህርት ቤት ነክ እንቅስቃሴዎች የነበረኝ ተሳትፎ፣ እንዲሁም የቤተሰቤ የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ መሆንም እድሉን እንዳገኝ አስተዋፅኦ ነበራቸው።



**ትማር፡ -** በፋዊ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ ፕሮግራም በመታቀፍሽ፣ ታገኚያቸው የነበሩትን ድጋፎች ብትገልጪልን?

**ዳግማዊት ፍቃዱ፡ -** በፋዊ ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሽፕ ፕሮግራም በመታቀፌ፣ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን አግኝቻለሁ። ፕሮግራሙ፣ ከእኔም አልፎ ቤተሰቤን የጠቀመ ፕሮግራም ነበር ብል ማጋነን አይሆንብኝም። ካገኘኋቸው ጥቅሞች መካከል፣ የንፅህና መጠበቂያ የተለያዩ ቁሶች፣ (የጥርስ ሳሙናና ብሩሽ፣ የገላና የልብስ ሳሙናዎች፣ የሴቶች ንፅህና መጠበቂያዎች/ሞይስ እና የመሳሰሉት)፣ ዩኒፎርም እና ጫማ፣ የጽህፈት መሣሪያዎች (ሁለት ደርዘን ደብተሮችና አስር አስር እስኪሪቢቶዎችና እርሳሶች) አጋዥ መጻህፍቶች (በሁሉም የትምህርት አይነቶች) እንዲሁም የትምህርት ቤት ቦርሳ በዋናነት የሚጠቀሱ ቁሳቁስ ናቸው።

በፕሮግራሙ ሌለው የተደረገልኝና በዋናነትም ልጠቅሰው የሚገባኝ፣ ለትራንስፖርት እንዲሁም ለሌሎች አስፈላጊ ነገሮች እንዳውለው ይሰጠኝ የነበረው ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ነው፣ ፡ በመሆኑም፣ ለተለያዩ ወጪዎች መሸፈኛ በየወሩ የ750 ብር ድጋፍ ሲደረግልኝ ነበር።

ስልጠናን በተመለከተ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋዬን እንዳዳብር በየዓመቱ ለ6ወር ያህል በሳምንት 3ቀን ቋንቋውን የተመለከተ የማሻሻያ ስልጠና በባለሙያዎች ተሰጥቶኛል፣ ፡ በየትምህርት ዓይነቱም የቲቶሪያል ፕሮግራሞችም ተመቻችተውልኛል፣ ፡ እንዲሁም፣ በኢንተርፕረነርሺፕ፣ በህይወት ክህሎት፣ በአይሲቲ እና በመሳሰሉት የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስጃለሁ።

**ትማር፡ -** በዚህ ፕሮግራም በመታቀፍሽ በትምህርት ተሳትፎሽ ረገድ ያመጣሽውን ለውጥ እንዴት ትገልጪዋለሽ? ያመጣሽውን ለውጥ ቀድሞ ከነበረሽ የትምህርት ተሳትፎ ጋር በማነፃፀር በዝርዝር ብትገልጭልን?

**ዳግማዊት ፍቃዱ፡ -** በዚህ ፕሮግራም በመታቀፌ በጣም ብዙ የሚባል ለውጦችን አምጥቻለሁ። በዚህም መሰረት፣ ፕሮግራሙ፣ የአስተሳሰብ አድማሴን እንዳሰፋ፣ በክፍል ውስጥ ያለኝንም የትምህርት ተሳትፎ በእጅጉ እንድጨምር አድርጎኛል። በዚህ ረገድ፣ ይሰጡኝ የነበሩት አጋዥ መጻሃፍቶች የነበራቸው እገዛ በጣም ከፍተኛ ነበር። ለትምህርት ተሳትፎዬም ሆነ ለውጤቴ መሻሻል አይነተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ፕሮግራሙ አካል በሆኑ ስልጠናዎች በመሳተፍ ያገኘኋቸው ለውጦች በቀላሉ የሚገለፁ አይደሉም። በህይወቴ ብዙ ለውጦችን እንዳመጣ የረዱኝ ናቸው። በዚህም መሰረት፣ ከቋንቋ አንፃር በእንግሊዝኛ የተሰጠኝ የማብቃት ስልጠና፣ በቋንቋው ከበፊቱ እጅግ በተሻለ ሁኔታ የመግባባት ችሎታዬን ማሳደግ ችያለሁ። አሁን ላይ ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር በሚገባ ተግባብቼ ማውራት እችላለሁ ብል ድፍረት አይሆንብኝም።

የህይወት ክህሎት ማዳበሪያ ተብለው የተሰጡኝ ስልጠናዎች ደግሞ፣ ህይወቴን እንዴት መምራትና ወደፊቴን እንዴት ማስቀጠልና ማስኬድ እንዳለብኝ በደንብ አሣውቀውኛል። እንዲሁም በእቅድ መመራት እንዳለብኝና አቅዶቼንም እንዴት ማሳካት እንዳለብኝ አስተምረውኛል።

ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ICT) አጠቃቀም ጋር የወሰድኩት ስልጠና፣ አሁን ላይ ያለኝን የኮምፒዩተር አጠቃቀም ክህሎት በከፍተኛ ደረጃ አሻሽሎልኛል።

**ትማር፡ -** ስለፕሮግራሙ ያለሽን አጠቃላይ አስተያየት በአጭሩ ብትገልጭልን?

**ዳግማዊት ፍቃዱ፡ -** ይህ ፕሮግራም፣ እጅግ ጠቃሚነት ያለው በጣም ጥሩ ፕሮግራም ነው። በተለይ ለእኛ ለሴቶች የሚኖረው ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው። ሴት ልጅ በአራሷ መተማመን እንዲኖራትና ከወንድ ልጅ እኩል የትኛውንም ነገር ማድረግ እንደምትችል ማስመስከር የምትችልበትን እድል መፍጠር የቻለ ፕሮግራም ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ ፕሮግራሙን በተመለከተ የማቀርበው አስተያየት አለኝ። እንደሚታወቀው፣ ይህ ፕሮግራም የሚያተኩረውና የሚተገበረው፣ ከ9-12 ባሉ የክፍል ደረጃዎች የሚማሩ ተማሪዎችን ብቻ የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ በማድረግ ነው። ነገር ግን፣ ሁለተኛ ደረጀ እያልን ለስኮላርሽፑ ፕሮግራም እንድንመረጥ ካደረጉን ነገሮች መካከል አንዱ የቤተሰባችን የኑሮ ሁኔታ እንደመሆኑ፣ በሁለተኛ ደረጃ ሲሰጠን የነበረው ድጋፍ የዩኒቨርስቲ ትምህርት ስንከታተልም ቢቀጥል መልካም ነው ብዬ አስባለሁ። ፡ ምክንያቱም፣ ዩኒቨርሲቲ ሲገባም በሴት ተማሪዎች ላይ የሚኖረው ጫና ከሁለተኛ ደረጃው የበለጠ ቢብስ እንጂ ያነሰ ነው የሚል ግምት ስለሌለኝ ነው። ለማንኛውም፣ ለሰጣችሁኝ መልካም ድጋፍ ግን አሁንም በእጅጉ አመሰግናለሁ።

**ትማር፡ -** ወደፊት መሆን የምትመኚውን ብትጠቅሽልን?

**ዳግማዊት ፍቃዱ፡ -** እኔ ወደፊት መሆን የምመኘው ነገር ቢኖር፣ የፊዚዮቴራፒ ትምህርት በመከታተል በሙያው ሀገሬንና ያሳደገኝን ህብረተሰብ ማገልገል ነው። ይህንን ምኞቴን እንደማሳካ ደግሞ በጣም እርግጠኛ ነኝ። በድጋሚ በፋዊ ኢትዮጵያ በኩል ለተደረገልኝ ድጋፍ ሁሉ ምስጋናዬን በዚህ አጋጣሚ አቀርባለሁ።

# ከአርአያዎች አንደበት

**ዶክተር ሰላም አክሊሉ፡ -** በሙያዬ ካይሮፕራክተር ነኝ። ካይሮፕራክቲክ የሚባለው የህክምና ሙያ ኒውሮ ማስኩላር እስኬሌተን ስፔሻሊስት ይባላል። ይህም፣ የነርቭ የጡንቻና የአጥንት በተለይም ደግሞ የአከርካሪ አጥንት ላይ የሚያተኩር አጠቃላይ የደህንነት ጤና አጠባበቅ ሙያ ነው። የተወለድኩት በድሬዳዋ ከተማ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን የተከታተልኩት ደግሞ ቤተርዳም በሚባል ትምህርት ቤት ነው። እናትና አባቴ ስምንት ልጆች ነበረቸው። የመጨረሻ ልጅ ስለነበርኩ በአስተዳደጌ ውስጥ ከእናትና ከአባቴ በተጨማሪ የታላላቆቼ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር። የሃይማኖት አባቶች እና አስተማሪዎቼም ዛሬ ላለሁበት ደረጃ ብርቱ ሚና ተጫውተዋል። በአርግጥ የመጨረሻ ልጅ በመሆኔ በርካታ ተንከባካቢዎች፣ አስተማሪዎች እና መካሪዎች የነበሩኝ ቢሆንም ከሁሉ በላይ ግን የአባቴ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር። ልጆቹን በጣም የሚያከብር፣ በአርጋታ የሚያዳምጥ ሃሳባቸውን የሚቀበል አባት ነበር። እኔም ይህንን ተጠቅሜ የህክምና ባለሙያ መሆን እንደምፈልግ ለአባቴ የነገርኩት ገና የስድስት ዓመት ልጅ ሆኜ ነው። እሱም "ትሆኛለሽ" አለኝ። "የኔ ልጅ ትችያለሽ" ተባልኩ። ይህም ፍላጎቴን ለማሳካት ብርታት ሆነኝ። ሁሌም የተመኘሁትን እንደምሆን ተስፋ እያደረግሁና ፍላጎቴን ለማሳካት ተግቼ እየሰራሁ ያሰብኩትን ለማሳካት ቻልኩ። "ትችያለሽ፣ ትችላለህ" የተባሉ ልጆች ይችላሉ። "The universe knows only one word and that word is yes." ዓለም ሁሉ የሚያውቀው አንድ ቃል "አዎ" የሚለው ነው። ከዛም ልጆች "ትችላላችሁ" ሲባሉ ዓለም ሁሉ ይሰማል ምላሹም አዎንታዊ ይሆናል። አዎን "ነህ ነሽ" የሚባልላቸው ልጆች ላይ የሚፈጥረው አዎንታዊ ተፅእኖ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ልጆችን እያበረታቱ ማሳደግ ለነገ እነሱነታቸው የሚኖረው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

**ደራሲና አርታኢ ሜሪ ጃዕፈር፡ -** ተወልጄ ያደግሁት በቀድሞ ኢሉባቡር ክፍለ ሃገር ጎሬ ከተማ ውስጥ ነው። አባቴ አቶ ጃዕፈር ሰይድ የየመን ዝርያ ያላቸው ኢትዮጵዊ ናቸው። እናቴ ደግሞ ወ/ሮ የስሚን አብርሃም ትባላለች፤ የግብፅ ዝርያ ያላት ኢትዮጵያዊ ናት። እናቴ አንድ ትምህርት ቤት የእጅ ሥራ መምህር ስለነበረች፣ የመደበኛ ትምህርት ቤት ከመግባቴ በፊት እናቴን ተከትዬ ትምርት ቤት እሄድ ነበር፣ ፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን የተማርኩት እዚያው ጎሬ አቡነ ሚካኤል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ቤተሰቦቼ በልጆች አስተዳደግ ጥብቅ የነበሩ ቢሆንም፣ እኔ ጨዋታና ዝላይ እወድ ነበር። በትምህርት ቤቱ ውስጥ በሚዘጋጁት የኳስ ጨዋታና የሩጫ ውድድር ዋነኛ ተሳታፊ ነበርኩ፣ ፡ በመሆኑም፣ የኔ ባህርይ ከቤተሰባችን አባላት ትንሽ ፈንገጥ ያለ ነበር። ሆኖም፣ በትምህርቴ ጎበዝ ስለነበርኩ፣ ይህ ባህርዬ ወላጆቼን ብዙም አላስከፋቸውም ነበር፣ ፡ እናቴም መምህርት በመሆኗ ሴት ልጅን ማስተማር ያለቀውን ጥቅም ታውቅ ስለነበር፣ እንድማር፣ እንዳነብ ትገፋፋኝ ነበር።። እኔም፣ ማንበብና መማር ያለውን ፋይዳ መገንዘብ የጀመርኩት ገና በልጅነቴ ነው።

ልጆች አድገው ጥሩ አንባቢና ጸሃፊ እንዲሆኑ፣ ወላጆቻቸው የሚነግሯቸው ተረቶችና ታሪኮች ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው። እኔም አሁን ላለኝ የድርሰት ሥራ መነሻ የሆነኝ ምንድን ነው ብዬ ወደኋላ ሳስብ ወደ አእምሮዬ ከሚመጡት ጉዳዮች የአባቴ ነገር ቀዳሚው ነው። በልጅነት እድሜዬ አባቴ በኔ ውስጥ የዘራው ዘር ይመስለኛል አሁን አድጎ ፍሬው የሚታየው። አባቴ ዘውትር ተረቶችን ያወራልኝ ነበር። በተለይ እንደነ አሊባባ ዓይነት የአረብ ተረቶች ሲነግረኝ ተመስጬ አሰማው እንደነበር ትዝ ይለኛል። አባቴ የሥነጽሁፍን ዘር ብቻ አልነበረም በእኔ ህይወት ውስጥ የዘራው። አባቴ ለትዳሩ ታማኝ፣ ከሚኖርበት አካባቢ ማህበረሰብ ጋር በመተሳሰብና በመፈቃቀር ያለውን ለሌሎች እያካፈለ የሚኖር ሰው ነበር። እና እኔም ታማኝነት፣ ፍቅር እና ሌሎች ማሰብን ከእርሱ ተምሬአለሁ።

**ወ/ሮ መሊካ በድሪ፡ -** ትውልዴ አዲስ አበባ ነው። ያደግኩትና ትምህርት የጀመርኩት ተክለሃይማኖት አካባቢ በተለምዶ በርበሬ በረንዳ በሚባለው ሥፍራ ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን አባድር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ደግሞ የካቲት 12 (የቀድሞ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት) ተከታትያለሁ። የ2ኛ ደረጃ ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ፣ የንግድ ሥራ ኮሌጅ በመግባት በባንኪንግ እና ፋናንስ በ1976 ዓ.ም. በዲፕሎማ ተመርቄያለሁ። ሥራ የጀመርኩት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጀማሪ የባንክ ክለርክነት ነው። ወደ ቀጣይ የትምህርት ደረጃ ለመዝለቅ ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበረኝ፣ ሥራ እንደ ጀመርኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማታው የዲግሪ ፕሮግራም ትምህርቴን ቀጠልኩ። በወቅቱ ትዳር የመመስረት ዓላማ ባይኖረኝም፣ ዘመኑ የሴት ልጅ ክብሯ ትዳሯ የሚባልበት ጊዜ ስለነበር፣ የጀመርኩትንም የዲግሪ ትምህርት ሳልጨርስ ወደ ትዳር ገባሁ።

ምንም እንኳን ፈጥኜ ትዳር ብይዝም፣ ትምህርቴን ከመቀጠል ግን አላገደኝም። የጀመርኩትን ትምህርት ለአንድ ሴሚስተር እንኳን ሳላቋርጥ ጨርሼ የመጀመሪያ ልጄን ከወለድኩ በኋላ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢኮኖሚክስ ዘርፍ አግኝቻለሁ። ሁለተኛ ዲግሪዬን ደግሞ፣ ከኦፕን ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ለንደን በManagement of Business Administration (MBA) አግኝቻለሁ፡ ፡ ለዚህ ጥንካሬዬና ብርታቴ መሰረት የሆኑኝ ወላጆቼ ናቸው። ያደኩበት ቤተሰቤ ሰፊ ነው። ደግነትን፣ ሃቀኝነትን እና ያላድሎ ማስተዳደርን በተግባር እያየሁ ነው ያደግኩት። ወላጆቼ በትምህርት ያልገፉ ቢሆኑም፣ ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡ ነበር። በዚህም ምክንያት በተለይም አንደኛ ደረጃ ትምህርቴን የደረጃ ተማሪ ሆኜ ነው የጨረስኩት።

**ወ/ሮ ዘሚ የኑስ፡ -** የተወለድኩት በአዲስ አበባ ከተማ ነው። እናትና አባቴ ፊደል ያልቆጠሩ ቢሆኑም፣ በተፈጥሮ የተማሩ በጥረታቸው የብዙ መልካም ውጤቶች ባለቤት የነበሩ ናቸው። አባቴ ጠንካራ እናት ያሳደጉት ከእረኝት ተነስቶ ታዋቂ የወንዶች ፋሽን ዲዛይነር ለመሆን የበቃ ነው። እናቴም ከገጠር የመጣች በልጅነቷ ተድራ ቤት የማስተዳደር ኃላፊነትዋን በአግባቡ የተወጣች፣ በልጅ አስተዳደግ፣ በቤት አያያዝና ቤቷን በጥበብ በመምራት ቤተሰቧን ለውጤት ያበቃች እናት ነበረች። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን የተከታልኩት ካቴድራል ትምህርት ቤት ነው። የኔ ቤተሰቦች ሙስሊሞች ናቸው። የተማርኩት ከብዙ ክርስቲያን ወንድሞቼና እህቶቼ ጋር ነው። እንደዚህ ዓይነት ስፍራ መማሬ ልዩነትን ለማወቅና ግልፅ አይታ እንዲኖረኝ ረድቶኛል። ስለሁሉም ለማወቅ እድል ሰጥቶኛል። የራስን ለማክበር የሌሎችንም እውቅና ለመስጠት አስችሎኛል።

ጥሩ ዜጎችን ለመፍጠር ሰርተን ማሳየት አለብን። በሥራችን ሌሎችን ማስተማር ያስፈልጋል። ገንዘብ ብቻውን ምንም ነገር አያመጣም። እኔ ያለ ሀገሬ፣ ሀገሬም ያለኔ ባዶ ነን ብለን ማሰብ አለብን። መከበርና ማደግ ከፈለግን ዛሬ መልፋት አለብን። ዛሬ ካልሠራን አይሆንም። ሰበብ አስባብ መቆም አለበት። ሰዓቱ አየሮጠ ነው።። መልካም ዜጋ ለማፍራት፣ ወላጆች መምህራንንና ታላላቆች ይህችን ጊዜ መጠቀም አለብን። መልካም ሆነን መልካምነትን የምናስተምረው ለማንም ስንል አይደለም። ለራሳችን ስንል ነው። እኛ ኢትዮጵያውን ጊዜ የለንም፤ ሌላው ቢዝናና ሰርቶ ነው። እኛ ግን ለነገ የማይባሉ በርካታ የቤት ሥራዎች አሉብን። በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ መስኮች ለመጪው ትውልድ ሰርተን የምናስረክባቸው ብዙ ሥራዎች ከፊታችን ይጠብቁናልና ሰርተን ማደግና ሥራንና ሥነምግባርን ማስተማር አለብን።

ምንጭ፡- "ፊልግ" በፊደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተዘጋጀ መጽሄት፣ ቁጥር ሁለት

# የትማር እንግዳ

**የትማር እንግዳችን ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ ይባላሉ። የፋዊ ኢትዮጵያ የደቡብ ብ/ብ/ሀ/ክ መንግስት ንዑስ ቻፕተር መሥራችና ሰብሳቢ ናቸው። ወ/ሮ ሙሉ፣ ንዑስ ቻፕተሩ በፋዊ ኢትዮጵያ ዓለማ መሰረት ጠንካራ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ከሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። በመሆኑም፣ እኚህ ባለሙያ የፋዊ ኢትዮጵያን እና የንዑስ ቻፕተሩን ጽ/ቤት እንቅስቃሴን፣ እንዲሁም የግል ህይወታቸውን በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጡን እንግዳ አድርገናቸዋል። እንደሚከተለው ቀርቧል።**



**ትማር፡-** ራስዎን ለአንባቢዎቻችን ቢያስተዋውቁ?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡-** ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ እባላለሁ። የትውልድ ስፍራዬ አነደጅር የሚባል አካባቢ ነው። 1960 ዓ.ም. የተወልድኩት። ባለትዳር እና የ8 ልጆች እናት ነኝ። አድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ያለውን የትምህርት ሂደት፣ በመካከል በመካከል በቤተሰቦቼ የሥራ ባህርይ የተነሳ፣ አንዳንድ የክፍል ደረጃዎችን በተለያዩ ክ/ሀገሮችና ዞኖች ብማርም፣ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በአብዛኛው የተማርኩትና ለወግ ማዕረግም የበቃሁት፣ በቀድሞው አጠራር በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በሲዳማ አውራጃ በዳሌ ወረዳ በምትገኘውና የብዙ ምሁራን፣ የዓለማ ፅናትን ከስነምግባርና ጓዳዊ ምስጢር ጠበቂነት ጋር ከተጎናጸፉት፣ ለፍትህ፣ ለነጻነት፣ ለእኩልነት፣ ለእውነት የወጣትነት ህይወታቸውን እስከሞት ከሰጡ፣ የቁርጠኝነትና የፅናት ባለቤት መናገሻ እና የጸሃፍት መፍለቂያ ከሆነችውና (ታላቁን ገጣሚ ደበበ ሰይፉን መጥቀስ ይቻላል) በህይወቴ ከውስጤ የማይጠፉ ብዙ የመኖር መሰረቶቼን ከተላበስኩባት በተወዳጇ፣ አንደ ስሟ ይርጋ ዓለም በሆነችው ከተማ ነው።

**ትማር፡-** አሁን ለደረሱበት ደረጃ መሰረት ሆኖሻል የሚሉት ምንድን ነው?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡-** አሁን ለደረስኩበት ደረጃ መሰረት በቅድሚያ የሆነኝ እግዚአብሔር ሆኖ፤ ቤተሰቦቼ፣ ባለቤቴ፣ የሥራ ባልደረቦቼና ጓደኞቼ፣ የፋዊ ኢትዮጵያ ማህበረሰብ በመለ እና በቅርበት የሚያውቁኝ ሁሉ ናቸው።

**ትማር፡-** በልጅነታችን ሁላችንም የምንመኘውን እንገልፃለን። ምኞትዎ ምን ነበር? ምኞቱስ ተሳክቶልኛል ማለትስ ይችላሉ?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡-** የልጅነት ምኞቴ፣ በድንግልና ምንኩስና ነበር። ይህ ግን፣ በቤተሰቦቼ ምክንያት ሳይሳካልኝ ሲቀር ወዲያው ኢንጂነር መሆን ፈለኩና የትምህርት ምርጫዬን ፕሮዳክቲቪቲ ቴክኖሎጂ አደረግሁ። በፍላጎቴ መሰረት እስከ አስረኛ ተምሬ ወደ ተግባረ እድ የመግባት ዕድል የገጠመኝ ቢሆንም፣ ትምህርቱ ግን ጅማ መሆኑ ሌላ ሳንካ ሆነብኝ። አሁንም ቤተሰቦቼ ፈቃደኛ ሳይሆኑልኝ ቀሩና እዛው ይርጋዓለም እስከ 12ኛ ድረስ በዛው መስክ አጠናቀቅሁ። ስለዚህ፣ እንደምኞቴ ሳይሆን በእግዚብሔር ፈቃድ የተሰጠኝ ሆነና "ወደምጠላው፣ ነገር ግን ለምን እንደምጠላው በተገቢ ምክንያት ወደማልገልፀው እና አንድም ቀን ለመሆን ወደማልፈልገው" ወደታላቁ ሙያ፣ በመምህርነት ለመሰልጠን ወደመምህራን ማሰልጠኛ ገባሁ። እንደሙያ ስልጠናው ሁሉ፣ ሌላውን ሁለተኛ ምዕራፍ ሳላጠፋ ጥላቻዬን ወደጎን ትቼ የመምህርነት ስልጠናዬን በሚገባ አጠናቅቄ መምህርት ሆንኩኝ።

**ትማር፡-** አሁን ለደረሱበት ደረጃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው የሚሉት ምንድን ነው?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡-** ያው ከላይ የገለጽኩት መነሻዬ ሆኖ፣ ዋናው ግን እልህና ቁጭት ነው። ለዚህ እንደምሳሌ የምጠቅሳቸው በርካታ ገጠመኞች አሉኝ። ለምሳሌ፣ መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት መምህር ሳለሁ፣ በራሴ ተነሳሽነት በተማሪዎች ላይ የምሰራቸው ሥራዎች ነበሩና፣ እነሱን ሥራዎች በትምህርት ሥርዓተ ትምህርት እንዲካተቱ ለመስጠት ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ። በመሆኑም፣ በአንድ ወቅት ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡ የትምህርት ባለሙያዎች ወደ ነበርኩበት ት/ቤት ሲመጡ፣ ርእሰ መምህሩ ፍላጎቴንና ዝግጅቴን ያውቅ ነበርና ባለሙያዎቹ ከእኔ ጋር እንዲገናኙ ያደርጓቸውል። ባለሙያዎቹ ይዘዋቸው በመጧቸውና የጽሁፍ ምላሽ በሚሹ የጽሁፍና የቃለ መጠይቆች መሰረት ተገቢውን ማብራሪያ ሰጠሁ። ባለሙያዎቹ በሰጠኋቸው መልሶች ከመገረማቸው የተነሳ፣ ከመጠይቃቸው ውጭ በግል በነበረን ውይይት "ይህን እንዴት አውቀሽ ሰራሽ? ከምን መነሻ? እስኪ መረጃሽ? ወዘተ." እያሉ ጠየቁኝ። ከዛም፣ በመረጃነት የያዝኳቸውን በማየትና ተማሪዎቼንም በማነጋገር፣ ስለመማር ማስተማር ሂደቱ መሻሻል መደረግ ስለሚገባቸው ጉዳዮች የበኩሌን ጥረት አደርግ እንደነበር ማረጋገጥ ቻሉ።

"በየክልሉ ዞረናል፤ ወደ ማጠናቀቁም ላይ ደርሰናል። ግን፣ እስከአሁን እኛ ለመሥራት ለምንፈልገው ተግባር ምለሽ ያገኘነው እዚህ ት/ቤት ነው በማለት ስልኬን (የቤቴንና የትምህርት ቤቱን) ይዘው ሄዱ። ከተወሰኑ ቀናት በኋላም፣ አዲስ አበባ ለሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ሥራ ተሳታፊ ሆንኩ።

ለሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ለመሳተፍ መምጣቴ፣ ሌላ አጋጣሚም ፈጠረልኝ። በወቅቱ ፋዊ ኢትዮጵያን በመመስረት ሂደት ውስጥ የነበሩ አህቶቼን ዓለማ የመረዳት እድል አገኘሁ። የመጣሁበትን ክልል መሰረት አድርጌም ይጠቅማል ያልኩትን ሀሳብ አካፈልኩ። በመሆኑም፣ በበጎ ፈቃደ ይህን የፋዊ ኢትዮጵያ ዓለማ መተግበር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ በክልሌ እንዳለ በማንሳት፣ እኔም የድርሻዬን ለመወጣት ፍቃደኛና ዝግጁ መሆኔን ለፋዊ አህቶቼ አረጋገጥኩላቸው፤ እንዲመጡም ጋበዝኩ። ይህንንም መሰረት በማድረግ በቀጣይ በተደረጉ የሃሳብ ልውውጦች፣ የፋዊን ዋና ጽ/ቤት ቅርንጫፍ በደቡብ ብ/ክ/መንግስት ደረጃ መክፈት የሚያስችል አስቻይ ሁኔታ መኖሩ ላይ ስምምነት መድረስ ተቻለ።

የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ መከፈት፣ በተለያዩ መልኩ እኔንም ጠቅሞኛል ብል ማጋነን አይሆንም። ሴቶች ወደ አመራርነት እንዲመጡ ተከታታይነት ያለው ስልጠና የማግኘት ዕድል ገጠመኝና ሰለጠንኩ። ከዛም፣ በፋዊ አዘጋጅነት በተከታታይ ከተሰጡት በነዚህ ስልጠናዎች ከተሳተፉት ውስጥ "ምን ያህሉ ወደ አመራር መጡ?" በሚል ርእሰ ጉዳይ ስልጠና ነክ ውይይት ነበር። በዚህ ውይይት ውስጥ ከተሳተፍን ውስጥ ባጋጣሚ ወደ አመራርነት ያልመጣን አንድ ሁለት ሴቶች ነበርን። በወቅቱ ያን ስልጠና እና ግምገማ ትመራ የነበረችው

ሴት እልህና ቁጭት የሚያሳድር ንግግር መናገሯን አስታውሳለሁ። ንግግሯ ከፍተኛ እልህና ቁጭት ነው ያሳደረብኝ:: በመሆኑም፣ "ውድድር ይምጣ እንጂ ዳግም አልወቀስም፤ ተወዳድሬ ርእሰ መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ሆኜ አሳያለሁ" ብዬ ለራሴ ቃል ገባሁ። በገባሁት ቃል መሰረትም፣ ውድድር ተወዳደርኩ፤ ውድድሩን በማለፍም ርእሰ መምህር ሆንኩ። እንደ ደቡብ ክልል በዛ ወቅት ስኬታማ ብቸኛ የ2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት ርእሰ መምህር የሚል ሜዳለያ ተሸላሚ መሆን ቻልኩ። በአሁኑ ወቅትም፣ የትምህርት ባለሙያ በመሆን እያገለገልኩ እገኛለሁ። ባጠቃላይ፣ ወደ አመራርነት እንድመጣ የረዳኝ አንዱ ፋክተር ነው ብል ማጋነን አይሆንም።

**ትማር፡ -** በትምህርቴም ሆነ በሥራዬ እንደ ትልቅ ስኬት የምቆጥራቸው ናቸው የሚሏቸውን ጉዳዮች አጋጥመውኛል ከሚሏቸው ተግዳሮቶች ጋር በማያያዝ ቢዘረዝሩልን።

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** በትምህርቴ ትልቅ ስኬት የምለው ያስተማርኳቸው ተማሪዎቼ ስኬታማነት ማየቴ ሲሆን፣ በሥራዬ ትልቁ ስኬቴ ነው የምለው ወደ ርእሰ መምህርነት ስመጣ፣ ትምህርት ቤቴ በሀዋሳ ከተማ ካሉ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል በተማሪዎች ሥነ-ምግባርና የትምህርት ውጤት ከፍተኛ ችግር ውስጥ የነበረበት ወቅት ነበር። በመሆኑም፣ አጠቃላይ በትምህርት ቤቱ መምህራን፣ ሠራተኞች እና በትምህርት ቤት አስተዳደር በኩል አስቸጋሪ የሥራ መስተጋብር የሚስተናገድበት፣ ርእሰ መምህራን የማይቆዩበት፣ ለአሠሪው መስሪያ ቤትም ፈተና የሆነበት፣ ህብረተሰቡ ደግሞ ት/ቤቱ ወደ መሰናዶ እንዲያድግ የነበረው ፍላጎት ከፍተኛ የሆነበት፣ የግብዓት ችግር ማነቆ የሆነበት ነበር። እነዚህን ከፍተኛ ችግሮች ለመፍታት የት/ቤቱ ርእሰ መምህራን፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ የተማሪ ወላጆች (አሳዳጊዎች) ባለድርሻ አካላት፣ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በጋራ ተቀናጅተን ተንቀሳቅሰናል። በርእሰ መምህርነቴ ባሳለፍኩባቸው 4 ዓመታት ከላይ የጠቀስኳቸው ችግሮች በየመልካቸው እንዲፈቱ ማድረግ ችያለሁ ማለት እችላለሁ። የችግሮቹ መፈታት፣ የትምህርት ቤቱን ደረጃ በማሳደግ የተማሪዎች ሥነ-ምግባር እንዲሻሻል፣ በየዓመቱም ያልጋሸበ ተከታታይነት ያለው የትምህርት ውጤት እንዲመዘገብ፣ ተማሪዎች በሃገር አቀፍ ደረጃ በሳይንስና ፈጠራ ሥራዎች የውድድሩ አሸናፊ እንዲሆን፣ በየትምህርት ዘመኑ ከአቻ ት/ቤቶች ጋር በከተማ ደረጃ በሚዘጋጁ የጥያቄና መልስና ስፖርታዊ ውድድሮች አብዛኛውን በአሸናፊነትና በአውቅና ትምህርት ቤቱ እንዲያጠናቅቅ አስችሏል። እነዚህ በርእሰ መምህርነቴ ያስመዘገብኳቸው ውጤቶች ስኬቶቼ ነበሩ ማለት እችላለሁ።

ከተግዳሮት አኳያ፣ እንደ እድል ሆኖ እንደሆነ አላውቅም፣ በየትኛውም የትምህርት እርከንና ደረጃ ስማር በአንዱም ያለ ተግዳሮት ያሳለፍኩበት ግዜ ትዝ አይለኝም። ለምሳሌ፣ እኔ የተማርኩባቸው ከ67-70ዎቹ ከነበሩ ከፖለቲካው ሁኔታዎች የተነሳ በወላጆቼ፣ በአካባቢ የነበረው ሰቆቃ፣ ከዛም በሴትነቴ በት/ቤት ውስጥ ከመምህራኖች፣ ከተማሪዎች ከት/ቤት ውጭም ከትንንሽ እስከ ትልልቅ ባለስልጣናትና ከታጣቂ ኃይል የነበረው ጸታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነበር። ይህን ተፅእኖ ቤተሰብ እንዳይከላከልልኝ፣ በወቅቱ ቤተሰቤ በተለይ እናቴ የማታዳምጠኝ የማትረዳኝ እና ያገጠመኝን ስናገራትም "አንቺ ባትስቂ፣ ፊት ባትሰጪ፣ አንገትሽን ብትደፊ፣ ወዘተ." በሚል እንደውም ለሌላ ቁጣና ቅጣት የምዳረግበትን ግዜ ሁሉ ባለስታውሰው ይሻለል። ለመጥፋት ሁሉ አሰብና፣ በድንግልና ስለመቆየት የተሰበኩት ስብከት መንገድ ላይ ቢገጥመኝስ----ብዬ እሱንም በመፍራትና በመቋቋም ጭምር ነው ዛሬ ላይ ለደረስኩበት ደረጃ መብቃት የቻልኩት።

**ትማር፡ -** የፋዊ ኢትዮጵያ ቻፕተር አባል መሆንዎ ይታወቃል። ቻፕተሩ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ለመሳተፍ ምን አነሳሳዎት? በግልዎ ምንስ ውጤት አግኝቼበታለሁ ይላሉ?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** ቀደም ብዬ እንደጠቀምኩት፣ በግሌ የተለየ ስልጠናና ድጋፍ ሳይኖርኝ፣ በራሴ ተነሳሽነት እና ያለምንም አስገዳጅ ሁኔታ የበጎ ፈቃድ ተግባር የማከናወን ጥረቱ ነበረኝ። የፋዊ ኢትዮጵያ ቻፕተር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ለመሳተፍ እንድነሳሳ ያደረገኝ በዋናነት፣ የማህበሩ ዓላማ እያከናወንኩ ለነበረው በጎ ተግባር አጋዥ ሆኖልኝ ማግኘቴ ነው። በተለይም፣ ማህበሩ ለሴት ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ማደግ የሚያደርገው ጥረት በተለየ ሁኔታ ስቦኛል ማለት እችላለሁ። ማህበሩ ከትምህርት መዳረስ ጋር በተያያዘ ያስገኘው ውጤት የኔንም ውጤት ነው ብዬ መግለፅ እችላለሁ። በግሌም ቢሆን የማህበሩ አባል በመሆኔ፣ የመምራት አቅሜን እንዳላጣ ካስቻለኝ አንዱ ከመሆኑም በላይ፣ ከሥራ ጓደኞቼ የመሪነትን፣ የመፍጠርን፣ የመዳኘትን፣ ባጠቃላይም የተለያዩ ችሎታዎችንና አቅምን አውጥቶ መጠቀመን እንድጋራ ረድቶኛል።

**ትማር፡ -** ፋዊ ኢትዮጵያ በሴቶች የትምህርት ዘርፍ በተለይም በአጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ ያደረገውን አስተዋፅኦ እንዴት ይገመግሙታል? በቻፕተሩ የሀዋሳ ቅርንጫፍ እያደረጉ ካሉት አሁናዊ ተሳትፎ ጋር በማገናዘብ ቢያብራሩልን።

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** ፋዊ ኢትዮጵያ፣ በሴቶች ትምህርት በቀድሞው ደቡብ ክልልና ሃዋሳ ከተማ አሁንም በሲዳማ ክልል በሃዋሳ ከተማ የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነትን ለማሳደግ ለመንግስት የትምህርት ፖሊሲ አጋዥ በመሆን ቀደም ሲል በነበሩት ፕሮጀክቶቹ ለሴት ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲመቻች በማድረግና የትምህርት ቁሳቁስ በማቅረብ፣ ባጠቃላይም ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቦናዊ ድጋፍ እና የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል። እንዲሁም ለሴት መምህራን የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በማመቻቸት፣ ለሥርዓተ ፆታ ክበባት የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ፣ በት/ቤቶች የሴት ተማሪዎችን ቤተ-መጻህፍትን በቁሳቁስ በማደራጀት እና የሴት ተማሪዎች መፀዳጃ ቤቶችን ግንባታ በማሟላት፣ አሁንም እየተከናወነ ባለው ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮጀክትም 70 ከመቶ ሴቶችን 30 ከመቶ ከሆኑ ወንድ ተማሪዎች ጋር በማካተት በትምህርት ክፍያ፣ በቁሳቁስ በመደገፍ፣ ከገጠር መጥተው ለሚማሩ እና መጠጊያ ቤተሰብ ለሌላቸው የቤት ክራይ በመሸፈን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ለሚደግፋቸው ተማሪዎች ተጨማሪ የማጠናከሪያ ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ የኢንግሊዘኛ ቋንቋ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በመዘርጋት፣ የአይሲቲ፣ የተለያዩ የአቅምና የሙያ ነክ ገቢ ማስገኛ ስልጠናዎች እንዲሰጡ በማድረግ፣ የሴት ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ከማሳደግ አኳያ ፋዊ ኢትዮጵያ እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም::

**ትማር፡ -** ለትምህርት ጥራት፣ በተለይም ለሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ማሳደግ፣ አሁንም ተግዳሮቶች ናቸው የሚሏቸውን ጉዳዮች መፍትሄ ይሆናሉ ከሚሏቸው ጉዳዮች ጋር አያይዘው ቢጠቅሱልን።

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** በትምህርት ጥራት፣ በተለይም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ በማሳደግ ረገድ አሁንም ያሉ ተግዳሮቶች፣ በተለይም

የቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አመለካከታዊ ችግሮች ፈቀቅ ያላሉ እንደመሆናቸው፣ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ለመሻገር በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ አጋዥ መሆን የሚገባቸው ባለድርሻ አካላት በሙሉ በመሰጠትና በተነሳሽነት አሁንም ጉድለቶች ይታዩባቸዋል። ስለሆነም፣ እነዚህ አካላት በመላ ራስን ካማከለ ስሜት በመውጣትና "እኔም ለችግሮቹ መቀረፍ ድርሻ ሊኖረኝ ይገባል" በማለት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡ ፡ እኛም የትምህርት ባለሙያዎች፣ እነዚህ አካላት ስለሚኖራቸው ተሳትፎ መጎልበት፣ የተለያዩ ስልቶችን በመቅረፅ በስፋት መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል።

**ትማር፡ -** በሃገራችን የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ከወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ደረጃ መሻሻልን እያሳየ ቢሆንም፣ አሁንም ተጨማሪ ጥረትን የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ አያጠያይቅም። ስለሆነም፣ ይህን በተመለከተ ከእስካሁኑ በተለየ መልኩ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** ምንም እንኳን የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ፣ ከወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ሲነፃፀር (በተለይ በመጀመሪያው የትምህርት እርከን ላይ) እንደ ክልላችን እና ከተማችን ተመጣጣኝ ደረጃ ላይ በመሆን ከፍተኛ መሻሻል የሚታይበት ቢሆንም፣ ከ2ኛ ደረጃና ከከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ አኳያ ሲታይ ግን ተጨማሪ ጥረት በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም። ስለሆነም፣ በዚህ የትምህርት እርከን የሚስተዋለውን የተሳትፎ ልዩነት ማጥበብ እንዲቻል፣ በነፃና ሙያዊ አይታና ልየታ ላይ የተመሰረተ፣ በሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ የተረጋገጠ ችግር ፈቺ የሆነ ጥናት ማካሄድና በጥናቱ መሰረትም ትክክለኛ የመፍትሄ አሠራርን ማፍለቅና ሥራ ላይ ማዋል ለነገ ተብሎ የማይተው ሥራችን ሊሆን ይገባል።

**ትማር፡ -** በሃገራችን በትምህርትም ሆነ በሥራ ላይ ያሉ ወጣት ሴቶች የስኬት ጎዳናቸውን እንዲያስቀጥሉና በሃገራችን ሁለንተናዊ አንቅስቃሴ ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲችሉ ምን ምን ተግባራት መከናወን አለባቸው ይላሉ?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** በሀገራችን፣ በትምህርትም ሆነ በሥራ ላይ ያሉ ወጣት ሴቶች የስኬት ጎዳናቸውን እንዲያስቀጥሉና በሀገራቸው ሁለንተናዊ አንቅስቃሴ ውስጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችሉ አመቺ ሁኔታዎች መኖራቸው እሙን ነው። ሆኖም፣ አሁንም በዚህ የስኬት ጎዳናቸው ላይ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች አሉ። ከገጠር አስከ ከተማ በሴቶች ላይ የተጫነውንና ቤተሰባዊ ሃላፊነትን ለሴቲቱ ብቻ የሚተወው የተዛባ አመለካከት፣ ባህላዊና ልማዳዊ አስተሳሰቦችንና አሠራሮችን መሰረት አድርጎ ዛሬም በስፋት መስተዋሉ አልቀረም። ስለሆነም፣ የየአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ ያደረጉና የሴቲቱን የሃላፊነት ጫና ሊቀርፉ የሚችሉ፣ ተግዳሮቶቻቸውን ሊያሻሽሉ የሚችሉአሠራሮችንመቀየስናመተግበር ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ፣ የሥራ ጫናዎቻቸውን የሚያቃልሉ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ አቅርቦት ማስፋፋት፣ የህፃናት ማቆያ ሥፍራዎች በመንግስት ተቋማት ጭምር እንዲስፋፉ ማድረግ፣ ከቤተሰብ ጀምሮ ያሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመለየት መፍትሄያቸውን በተመለከተ ከእስካሁኑ የበለጠ ሥራ መሥራት እና የመሳሰሉት ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲከናወኑ ማድረግ ይጠቅማል። በተለይም፣ በሴቶች የትምህርት ስኬታማነት ላይ ተግዳሮት ናቸው የሚባሉ ጉዳዮችን እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በትክክል በመለየት ከእነመፍትሄዎቻቸው ለመንግስትና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ማቅረብ የሚችል ጥናት ማካሄድ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ የሚቀመጡ ሴቶችን መጠን ማመጣጠን የሴቶችን ሁለንተናዊ አንቅስቃሴ በማጎልበት ረገድ የራሱ ጠቀሜታ አለውና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

**ትማር፡ -** ወጣቶች፣ በትምህርታቸውም ሆነ በሥራቸው ላይ የላቀ ደረጃ ላይ ደርሰው ለሃገራቸው የሚጠቅሙ ዜጎች እንዲሆኑ፣ ልምድዎንና እውቀትዎን መሠረት በማድረግ ምን ምክር ይሰጣሉ?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** ወጣቶች፣ በትምህርታቸውም ሆነ በሥራቸው ላይ በለቀ ደረጃ ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በሚፈለግባቸው ልክ ለማገልገል እንዲችሉ፣ ቀና አስተሳሰብንና አመለካከትን፣ ስክነትንና አርቆ አሳቢነትን፣ ለሌሎች መኖርንና በጎ ፈቃደኝነትን፣ ነገሮችን መመርመርንና ማመዛዘንን ማጎልበት አለባቸው። ለዚህ ደግሞ፣ በመደመር አስቤ የመሰጠት፣ ተጨማሪ ማዜን፣ ጉልበትንና እውቀትን፣ ተዓማናዊ እውነቶችን ላይ በመመስረት የመተግበር ተነሳሽነት ሊኖራቸው ይገባል። ሁለንተናዊ ስብዕናቸውን (ሰው መሆንና በተጸፈልን ልክ እንደሰው መኖርን) በማብዛት፣ እውቀታቸውን የማካፈል፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ለሃገር ግንባታ የመስጠትና የማካፈል እሳቤ ያጎለበቱ፣ ሰው ሁን በተባሉት ልክ ሆነው መገኘትን ማዳበር አለባቸው። ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከቂመኝነት፣ ከክፋ ብድራት ከፋይነትንና ከፋፋይነት፣ ከተፈቀደላቸው / ከሚገባቸው/ በላይ ሰብሳቢ ከመሆን መራቅ ይጠበቅባቸዋል። ውሸትን፣ አስመሳይነትን፣ሌብነትን፣ ያሉበትን ባለሆኑ መሳብን፣ በማይጠቅም ትርክት ጎጅነትንና ምቀኝነትን፣ ያልተሰጠን መሻትን፣ ፀብ ጫሪነትን፣ መናናቅና አለመቀባበልን መጠየፍ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ፣ ወጣቶች በሚያገኙት ላይ ብቻ ሳያተኩሩ፣ በሚያስገኙት ነገር ላይም በስፋት በመገንትና በመሰማራት የመኖር መርህን ዋና የህይወታቸው አካል አድርገው ለህይወታቸው ስኬት ዘውትር እንዲተጉ፣ በተጨባጭ በህይወቴ ያስተዋልኩትን ተንተርሼ ለወጣቶች ምክሬን አለግሳለሁ።

**ትማር፡ -** የአረፍት ጊዜዎን በምን ያሳልፉሉ?

**ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፡ -** የሚኖረኝን የአረፍት ጊዜ በአብዛኛው የማሳልፈው፣ ማህበራዊ በሆኑ ጉዳዮች በመሳተፍ፣ ወደአምነት ቦታዎች/ቤተክርስቲያን በመሄድ፣ የቤቴን ጉዳዮች በመከወን ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ የሚኖረኝን ጊዜ እንደሁኔታው በማመቻት ለነገ ሥራዬ በመዘጋጀት፣ መጣጥፎችን በመጸፍ፣ በማንበብ፣ ፊልሞችን እና ድራማዎችን በማየት፣ ወዘተ. ነው።

## ቀልዶች

### ክብደት የመቀነስ ዘዴ

እንዴት እንዴት ሸነቀጥሽ ባክሽ!

ባሌ ሌላ ሴት ጋር እየሄደ ሲያንገበግበኝ፣ ሲያበግጎኝ...

አውነትሽን ነው? በቃ ተፋታችሁ ማለት ነው?

አልተፋታንም። ገና የምቀንሰው አንድ ሶስት ኪሎ ይቀረኛል።

### አሃ ለዚህ ነዋ!

ሰውየው አሳ እያጠመደ እያለ፡ -

ፖሊስ፡ - የኔ ወንድም እዚህ ቦታ ላይ አሳ ማጥመድ ክልክል ነው።

አሳ አጥማጅ፡ - አሃ! ለዚህ ነዋ! ሶስት ሰዓት ሙሉ አንድ እንኳን አሳ ያላጠመድኩት።

****

ቁም ነገር መጽሄት ሐምሌ 2000 ዓ.ም.

## ልዩ ልዩ ታሪካዊ ክንውኖች

✓በኢትዮጵያ አቪዬሽን የተጀመረው፣ ንጉሥ ተፈሪ ከገዟቸው ሦስት ፈረንሳይ ስሪት ፓቲዝ አይሮፕላኖች አንደኛዋን ፈረንሳዊው ሙሴ አንድሪ ማዮ ከጅቡቲ በማብረር ነሐሴ 12 ቀን 1921 ዓ.ም. ሥጋ ሜዳ (ገፈርሣ የመጠጥ ውሃ ማጣሪያ አካባቢ የሚገኝና በኋላ ታጠቅ በመባል ይጠራ የነበረ ስፍራ) አውሮፕላን ማረፊያ ከቀኑ 7፡10 ደቂቃ ላይ ባሳረፈበት ወቅት ነው። በኢትዮጵያ አቪየሽን ታሪክ የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያንአውሮፕላን አብራሪዎች ደግሞ፣ አስፋው ዓሊና ሚሸባ ባቢሸፍ (በአባቱ ሩሲያዊ በእናቱ ኢትዮጵያዊ) ናቸው። ሁለቱም የብቻ በረራቸውን ያካሄዱት በ1923 ዓ.ም. ነበር።

✓እ.ኤ.አ በ1935 ዓ.ም. የታተመው የአሜሪካ ጋዜጣ ስናፒ ላንዲንግ ሌዲ በርድ የሚል አድናቆት የሰጣቸው ወ/ሮ ሙሉ እመቤት አምሩ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ሴት አውሮፕላን አብራሪ ናቸው። የመጀመሪያውን የብቻ በራሪ ያካሄዱት ደግሞ በ1927 ዓ.ም ነበረ::ወ/ሮ ሙሉአመቤትን አውሮፕላን መንዳት ስተማር በታሪክ የመጀመሪያዋ አፍሪካዊትም እንዲሆኑ ያስቻሏቸው ኮለኔል ጄ.ሲ. ሮቢንሰን የተባሉ ጥቁር አሜሪካዊ ናቸው።

✓በኢትዮጵያ አቪየሽን የተጀመረው ንጉሥ ተፈሪ ከገዟቸው ሶስት ፈረንሳይ ስሪት ፓቲዝ አይሮፕላኖች አንደኛዋን ፈረንሳዊው ሙሴ አንድሪ ማዮ ከጁቡቲ በማብረር ነሀሴ 12 ቀን 1921 ዓ.ም. ሥጋ ሜዳ አውሮፕላን ማረፊያ (ከአዲስ አበባ በስተምአራብ ገፈርሣ የመጠጥ ውሃ ግድብ የሚገኝ) ከቀኑ 7:00 ላይ ባሳረፈበት ወቅት ነው። አይሮፕላኗም ንስረ ተፈሪ ተብላ ተሰየመች። በዚህን ጊዜ ህዝቡ አዲሱን የቴክኖሎጂ ውጤት እንዲህ በማለት ተቀበለው። "አውሮፕላን መጣ ሰማይ ለሰማይ የተበደለውን ደሃውን ሊያይ።"

✓የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የአየር መንገድ ጀት አብራሪ የሆኑት ካፒቴን አለማየሁ አበበ ናቸው። ጊዜውም ታህሣሥ 1949 ዓ.ም. ነው። እኚህ ሰው ከአፍሪካም የመጀመሪያው የንግድ ጀት አብራሪ እንደሆኑ ይታወቃል።

✓የኢትዮጵያ የባቡር ሐዲድ የመዘርጋቱ ሥራ በ1890 ሕዳር 22 ቀን ጅቡቲ ላይ የተጀመረ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ባቡር ከጅቡቲ ተነስቶ በ1893 ዓ.ም. ሐምሌ 15 ቀን ከኢትዮጵያ ግዛት ደወሌ ደረሰ። የጅቡቲ አዲስ አበባ የባቡር ሀዲድ የቴሌግራፍ መሥመር ከአፄ ምኒልክ ሞት ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ሥራው ግንቦት 30 ቀን 1907 ዓ.ም. አቃቂ የደረሰ ቢሆንም፣ ቀሪው ሥራ ከአቃቂ አዲስ አባባ ተዘርግቶ የምድር ባቡር አገልግሎት ሰኔ 4 ቀን 1909 ዓ.ም. ሥራ ጀመረ፣ ፣ የባቡር ሥራው ሰባት ሚሊዮን ብር ወጪ እንደፈጀ ተዘግቧል።

✓ማዘጋጃ ቤት፣ "ማህበር ቤት" ተብሎ በ1903 ተቋቋመ። ቦታው ፒያሳ የምኒልክ ሀንፃ እየተባለ በሚጠራው ውስጥ ነበር። በኋላ አሁን አውራጃ ፍርድ ቤት ወደሆነውና ቀድሞ የነጋድራስ ኃይለጊዮርጊስ ቤት ወደነበረው ፎቅ በ1908 ተዛወረ። የመጀመሪያው ከንቲባም ቢትወደድ ወልደፃድቅ ነበሩ።

ምንጭ፡- ቴዎድሮስ በየነ፣ ኅብረ ኢትዮጵያ፣ 1999 ዓ.ም.

## የእናት ዘመን

በጥንት የጋርዮሽ ህብረተሰብ፣ ጋብቻ በአንድ ወንድና ሴት የተወሰነ ስላልነበር፣ ሁሉም ወንድ ከሁሉም ሴት፣ ሁሉም ሴት ከሁሉም ወንድ ግንኙነት ስለሚኖራቸው ልጆች አባታቸውን አያውቁም ነበር። ይህ ዘመን የእናት ዘመን ይባል ነበር። የእናት ዘመን ካሰኘው ምክንያት አንዱ ሴቶች የህብረተሰቡ የኢኮኖሚ አውታር በመሆናቸው፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ልጆች አባታቸውን ባለማወቃቸው ዘር የሚቆጠረው በእናታቸው ወገን ስለሆነ ነበር።

ሐምራዊ መጽሄት፣ መጋቢት 2002 ዓ.ም.

## የቋንቋዎች መወራረስ

| ግዕዝ | ዕብራይስጥ | አረብኛ | አማርኛ |
|---|---|---|---|
| ገመል | ጋማል | ጀመል | ግመል |
| አኅት | አሖት | ኡኅት | እህት |
| ድብ | ዶብ | ዱብ | ድብ |
| አዳማ | አዳማ | | ቀይ መሬት |
| እዝን | አዜን | ኡዝን | ጆሮ |
| አልፍ | ኤሌፍ | አልፍ | አልፍ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ብእር | ብዔር | በዔር | በሬ |
| ደብተር | ደፍተር | ደፍተር | ደብተር |
| ደም | ዳም | ደም | ደም |
| ዝአብ | ዝኢብ | ዚኢብ | ጅብ |

ምንጭ፡- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ

## ልጆች የፍቅርም የጠብም መንስኤዎች

አብዛኞቻችን፣ ልጆች ትዳር እንደሚያሞቁ እና የባልና ሚስቱን ፍቅር እንደሚጨምሩ እንጂ፣ ትዳርን ሊበጠብጡ እንደሚችሉ አናውቅም። ነግር ግን፣ በልጆች አስተዳደግ ላይ ጥንቃቄ ካላደረግን፣ ልጆች ዋነኛ የጠብ መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ።

በወላጆች መካከል የአመለካከት ልዩነት እንዳለ ልጆች ካወቁ፣ ልዩነቱን ተጠቅመው ፍላጎታቸውን ለማሳካት ይጥራሉ። አናታቸው የከለከለቻቸውን አባታቸውን አስፈቅደው፣ አባታቸው የከለከላቸውን እናታቸውን አስፈቅደው ፍላጎታቸውን ለማሳካት ይጥራሉ። በዚህ ወቅት፣ አናትና አባት፣ "እኔ የከለከልኩትን ለምን ፈቀድክ ? ለምን ፈቀድሽ? ልጄን አበላሸሽ! አበላሸህ!" በሚል ለጠብ ይጋበዛሉ።

በአንዳንድ ወላጆች ዘንድ እንደሚስተዋለው፣ ልጆች የሆነ ነገር ለማድረግ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ እናት "ሂድና አባትህን ጠይቅ!" አባትም፣ "ሂድና እናትህን ጠይቅ!" የሚል ምላሽ ይሰጣሉ። እንዲህ ያለው ምላሽ ስህተት ነው። ለልጆች የሚሰጠው ትርጉምም፣ "እኔ ስለምወድህ እፈቅድልሃለሁ። አባት/ እናትህ ግን መጥፎ ስለሆነ/ ስለሆነች ይከለክልሃል" እንደማለት ነው። በተቃራኒው፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ማለት ያለባቸው፣ "ይህንን ጉዳይ እኔና አባትህ ተነጋግረንበታልና አይሆንም ወይም ከአባትህ ጋር ተነጋግረን በኋላ እነግርሃለሁ" የሚለውን ነው። ባጠቃላይ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ አንድ መሆን አለባቸው። የአነርሱ አንድነት፣ ልጆችን ለሁለቱም እኩል ፍቅርና ክብር እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል።

ምንጭ። ዘመን መጽሄት፣ ግንቦት 2004 ዓ.ም.

## የፋዌ ኢትዮጵያ ስኬት አንዱ ማሳያ

ርእሱ እንደሚጠቁመው፣ በፋዌ ኢትዮጵያ የCSSP-" Beyond Numbers: Towards Gender Transformation" የሚለው ፕሮጀክት፣ ዶታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን በመከላከል እና የሴቶችን ፖለቲካዊ እና ውሳኔ ሰጪነት ሚናን በማጎልበት ላይ ትኩረት በማድረግ የሚከናወን ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ፣ በአማራና በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ሰሜን ሸዋ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ በደብረ ብርሃን ከተማ፣ በሸኖና በአሌልቱ ወረዳዎች ውስጥ እየተከናወነ የሚገኝ ሲሆን፣ በርካታ አዎንታዊ ውጤቶች ተመዝግበውበታል። የፕሮጀክቱ ስኬት ተደርገው ከሚቆጠሩት ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ፣ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግሥት ሰሜን ሸዋ ዞን አሌልቱ ወረዳ ውስጥ በሚገኘውን ጮሌ ሰንከሌ ቀበሌ ውስጥ የተገኘው ውጤት እንደማሳያ እንደሚከተለው ቀርቧል።

እንደሚታወቀው፣ የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ፣ ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው አካባቢዎች በሴቶች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ሚና ኖሯቸው በእንቅስቃሴያቸው ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ አካባቢ ተኮር ድርጊቶች እንዲቀረፉ አስቻይ ተግባራትን ማከናወን ነው። በዚህ ረገድ፣ የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማሻሻል እና የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን ማጎልበት፣ የሚስተዋሉ ዶታዊ ጥቃቶች እንዲቀንሱ ማድረግ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

በዚህምመሰረት፣ በአሌልቱ ወረዳየሴቶች፣ የህፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በጮሌ ሰንከሌ ቀበሌ በሴቶች ላይ የሚስተዋሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ በአጠቃላይም የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ከማጎልበት ጋር በተያያዘ ለማከናወን የያዘውን እቅድ መተግበር እንዲችል፣ የፋዌ ኢትዮጵያን ድጋፍ ጠይቋል። ወረዳው ያዘጋጀው እቅድ በዋናነት ያተኮረው፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ ጠለፋን፣ አስገድዶ መድፈርን፣ የሴቶች ግርዛትን፣ እና የመሳሰሉትንና ሌሎች በሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖራቸዋል ብሎ የለያቸውን ጉዳዮች ላይ ነው። ፋዌ ኢትዮጵያ፣ በራሱ በኩል ባደረገው ዳሰሳም፣ በእርግጥም እነዚህ አሉታዊ ድርጊቶች በቀበሌው ብሎም በወረዳው በስፋት የሚስተዋሉ እና ርብርብ ሊደረግባቸው እንደሚገባም በመረዳቱ፣ ተገቢውን እገዛ ለማድረግ በማህበረሰብ ተኮር የCSSP-2 ፕሮጀክቱ አማካይነት ተንቀሳቅሷል።

የአሌልቱ ወረዳ የሴቶች፣ የህፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በእቅዱ መሰረት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶቹ እንዳይስፋፉ ብሎም እንዲጠፉ፣ ህብረተሰቡ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችልበትን እቅድ አውጥቶ ተንቀሳቅሷል። በዚህ ረገድ፣ በህብረተሰቡ ዘንድ አንቱታን ያተረፉ ታዋቂ ሰዎችን፣ ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ በማሰባሰብ ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶቹ መቀረፍ ብሎም መወገድ ዓይነተኛ ድርሻ የሚኖረው አካባቢ ተኮር ልማዳዊ ህግ (Customary Law) እንዲቀረፅ የያዘው እቅድ ይጠቀሳል። ይሁንና፣ ይህን በበጎ ዓላማ ላይ የተመሰረተውን እቅዱን እውን ማድረግ እንዳይችል የተለያዩ ችግሮች እንቅፋት ሲሆኑበት የቆዩ ሲሆን፣ ከዚህ አኳያ አስፈላጊውን ገንዘብ በሚሟላት በኩል ያጋጠመው ችግር በዋናነት ይጠቀሳል። ወረዳው፣ ያጋጠመው የገንዘብ ችግር፣ ልማዳዊ ህጎቹ እንዲቀረፁ የሚያስችሉትንና የአካባቢውን ህብረተሰብ ያሳተፉ የተለያዩ የውይይት መድረኮች እንዳይዘጋጁ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል።

ፋዌ ኢትዮጵያ፣ ከፍ ተብሎ በተጠቀሰው መሰረት ይህን የወረዳውን ተግዳሮት ባገናዘበ መልኩ የበጎ ዓላማው ተጋሪ የሆነ እንቅስቀሴ አድርጓል። በወረዳው እቅድ መሰረትም፣ በጮሌ ሰንከሌ ቀበሌ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል በሚል እንዲረቀቅ የታቀደው አካባቢ ተኮር ልማዳዊ ህግ እውን እንዲሆን የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ በCSSP-2 ፕሮጀክት አማካይነት ተደርጓል። በዚህም መሰረት፣ ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች የተውጣጡ ታዋቂ ሰዎችን፣ ሽማግሌዎችንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያሳተፉ የተለያዩ መድረኮች የተካሄዱ ሲሆን፣ በመድረኮቹም ላይ በመገኘት፣ ከወረዳውና ከፋዌ ኢትዮጵያ የተውጣጡ ባለሙያዎች ሙያዊ እገዛ አድርገዋል። በተካሄዱ የተለያዩ መድረኮችም ሰፋ ያለ ውይይት በማድረግ፣ ልማዳዊ ህጉን ማዘጋጀትና ለወረዳው ማቅረብ ተችሏል።

የተዘጋጀው ልማዳዊ ህግም፣ ፀድቆ ሥራ ላይ መዋል እንዲችል፣ ህጉን የማፅደቂያ ፕሮግራምም፣ የፋዌ ኢትዮጵያ ባለሙያዎችን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ሚያዚያ 25 ቀን 2021 ዓ.ም. ተካሂዷል። ህጉን የማፅደቂያ ፕሮግራምም ያለምንም ችግር እንዲከናወን እንደተለመደው፣ ፋዌ ኢትዮጵያ የገንዘብና የባለሙያ ድጋፍ አድርጓል። የልማዳዊ ህጉ መፅደቅ፣ ህጉን በመተግበር ረገድ ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍሎች ለአንድ ዓላማ በጋራ እንዲንቀሳቀሱ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል። በዋናነትም፣ ሴቶች በአኗኗራቸው ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ አሉታዊ ድርጊቶችን በተመለከተ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አቅም የሚሆናቸው ከመሆኑም በላይ፣ እነሱን በተመለከተም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የሚኖራቸውን የውሳኔ ሰጪነት ሚና በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያጎለብተው ይጠበቃል።

## አዘን ብለህ ከጅብ ለቅሶ አትሂድ

ጅብና አህያ አበልጅ ሆኑ። ከአለታት አንድ ቀንም የጅብ ልጅ ታሞ ሞተ። አህያም "ያበልጄን ለቅሶ አልበለ" ብሎ ወገኖቹን ሰብስቦ ወደ ሀዘኑ ቦታ ሄደ። አያ ጅቦም አመስግኖና ያዘነ መስሎ "ዘመዶቼን የምሸኝበት እዝን ነገር ስጡኝ" አለና ጠየቀ፣ አህዮችም "ምን ዓይነት እዝን እንስጥህ?" አሉት። ጅብም "በቃ የላይኛውን ከንፈራችሁን ብቻ እየገነጠልኩ ልውሰድ" አለ። አህዮችም እንቢ እንዳይሉ ዝምድና ማፍረስ ሆነባቸውና "እሺ ይሁን" አሉና የላይኛውን ከንፈራቸውን እያስጎመዱ ሰጡ። በዚህ አልበቃም እና ጅብ "አመሰግናለሁ፤ ግን እዛ ማዶ ስትደርሱ ዙራችሁ ተሰናበቱኝ" አላቸው። አህዮቹም እንደተባሉት አደረጉ። ሲዞሩ የላይኛው ከንፈር ስለተጎመደ ጥርሳቸው በረዶ መስሎ ይታያል። ይሄኔ የጅብ ሀሳብ ተሳካና ዘመዶቹን ይዞ እየሮጠ ደርሶ የእያንዳንዱን አህያ ሆድ መቦትረፍ ጀመረ። አህዮችም ፣ "እንዴ ምን አደረግን? ምን ነው ምን አጠፋን አያጅቦ?" ሲሉ ጠየቁ። ጅብም፣ "ምን አደረግን ትላላችሁ እንዴ! የእኔ ልጅ ሞቶ እናንተ ትስቃላችሁ?" የሚል የማይረባ ተልካሻ ምክንያት ሰጠ።

ምን አለ አዚያው እያሉ ያንን ሁሉ አህያ ባንድ ጊዜ ከሚጨርስና ዘራቸውን ከሚያጠፋ "እጣ ተጣጥላችሁ አንድ ወይም ሁለት አህያ ለእዝን ስጡኝ" ቢላቸው!! ጅብ ማለት እንዲህ ነው። አዘን ብለህ አትራራለት። ልጅ ሞተው ብለህ ለቀሶ አትድረስለት።

ምንጭ፡የፍትህ መጽሄት እትም

## በወግ አዋቂው በመስፍን ሃብተማርያም እና በታዋቂው አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ መካከል የተደረገ ውይይት

**መስፍን፡-** አስቲ በዚያን ዘመን ስለነበረህ የዘፈን ልምድህ ወይም ውሎህ አጫውተኝ፡፡

**ጥላሁን፡-** ሠርግ፣ ሆያሆዬ...ከጓደኞቼ ጋር አሳተፋለሁ፡፡ ቲያትር ላይ አሳዛኝ ዜማ በል ይሉኛል....ቀረርቶ የማይቀር ነው፡፡ ልዑል መኮንን ኃይለሥላሴ የመጡ ጊዜ (ወሊሶ) ቀረርቶዬን ሰምተው አዲስ አበባ እንድትመጣ ብለውኝ ነበር፡ ፡ ብቻ ባጠቃላይ ማንጎራጎር ከልጅነቴ ያለተለየኝ ባህርይ ነበር፡፡

**መስፍን፡-** ወላጆችህ አይቃወሙህም ነበር?

**ጥላሁን፡-** እንዲያውም! ያደግኩት ከአያቴ ቤት ነው፡፡ አሳቸውንም ቁጣ ቁጣ ሲላቸው በዜማዬ አስረሳቸው ነበር፡ :

**መስፍን፡-** ኢዮኤል ዮሐንስ አበረታቶሃል የሚባለውስ?

**ጥላሁን፡-** አዎ! ሃገር ፍቅሮች በመጡ ጊዜ (ወሊሶ) አዲስ አበባ ና ብሎኝ ለመኮብለል አነሳስቶኛል፡፡

**መስፍን፡-** ያደረግከው ሙከራ ነበር?

**ጥላሁን፡-** አዎ! ቱሉ ቦሎ ድረስ በእግሬ አስከ መሄድ ደርሼ ነበር፡፡ ከዚያ አዲስ አበባ ልሄድ ስል የሚያውቀኝ ሰው ይዞ መለሰኝ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ሸራ ባለው መኪና አዲስ አበባ ደርሼ አክስቴ ቤት ዶሮ ማነቂያ ሄድኩ፡፡ አሷም አያቴ ጋር ወሊሶ መለሰችኝ፡፡

**መስፍን፡-** እና እንዴት ተሳካልህ ታዲያ?

**ጥላሁን፡-** በሶስተኛው ሙከራዬ ተሳካልኝና ሃገር ፍቅር ተቀጠርኩ፡፡ ይሄው ነው፡፡

**መስፍን፡-** ከዚያ ምን ምን ዘፈን ተጫወትክ?

**ጥላሁን፡-** እነ ጥላ ከለላዬን፣ አልማዝ ነሽ የጠራች መስታወት፣ የኔ ውብ ዓይናማ ....እና የመሰሰሉት፡፡

**መስፍን፡-** እዚያ በወጣትነትህ ፍቅር ይዞህ እንደነበር ሰምቻለሁ....እስቲ ስለእሱ አጫውተኝ...

**ጥላሁን፡-** ቀ/ኃ/ስ...ቲያትር ተወዛዋዥ ከነበረች ልጅ ጋር ፍቅር ይዞኝ ነበር፡ ፡ ሱዳን ሃገር ከቡድኑ አባላት ጋር ሄዳ ስትመለስ ሌላ ሰው መሃላችን ገባ፡፡ በቃ ....አፍላ እድሜ ላይ ስለነበርኩ በጣም ተበሳጨሁ፡፡

**መስፍን፡-** እና...እንዴት ተወጣኸው?

**ጥላሁን፡-** ተበሳጭቼ ስለነበር አቺዶ (አሲድ) ጠጣሁና ሆስፒታል ታክሜ ዳንኩ፡፡ በመጠኑ ባይሆን እሞት ነበር፡፡ ከዚያ ረሳኋት፡፡

**መስፍን፡-** ወደክብር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል እንዴት ተዛወርክ?

**ጥላሁን፡-** ሻምበል አውግተነው የሚባል ሰው ነው የወሰደኝ፡፡

**መስፍን፡-** ክብር ዘበኛ ከገባህ በኋላ በጀነራል መንግስቱ ንዋይ ትእዛዝ የወታደር ዩኒፎርም ትለብስ ነበር አሉ፡፡ ጥላሁን ገሠሠ ሲቪል ነው ወታደር ነው የሚል ያልተረጋገጠ ወሬ ሲነፍስ እኔም አስታውሳለሁ፡፡

**ጥላሁን፡-** በርግጥ አቶ መኮንን ሀብተወልድ ወደ ሃገር ፍቅር እንዳይመልሱኝ ለማድረግ በጀነራል መንግስቱ ትእዛዝ ለሶስት ወር ያህል የወታደር ዩኒፎርም ለብሻለሁ፡፡ በኋላ ግን ወደ ሲቪልነት ተመልሻለሁ፡፡

**መስፍን፡-** እንዴት? ጀነራል መንግስቱ ፈቅደውልህ ነው?

**ጥላሁን፡-** አይደለም፡፡ ሥነስርዓት አበላሽ ተብዬ ተመከርኩ፡፡ በዩኒፎርም ሆነህ እጅ ከነሳህ ሲቪል ስለምትመሰል ጃንሆይ መጥተው ሲጎበኙ፣ እንደዛ አድርግ ብሎ አንድ ሰው ሹክ ስላለኝ እንደተባለው አደረግኩ፡፡ ከዚያ ንጉሰ ነገስቱ ሲጎበኙ፣ የወታደር ሰላምታ በመስጠት ፋንታ እጅ ነሳሁ፡፡ ጀነራሉ ያዋረድኳቸው ዓይነት ሆኖ ተሰማቸውና "ድምፁን ተዉለትና ይህን ዩኒፎርም ግፈፉት አሰዳቢ ነው፡፡" አሉ፡፡ እኔም እንደምፈልገው ሆነልኝ፡፡ ጥይት ተኩሼ የማለውቀው ሰውዬ ወደ ሲቪል ህይወቴ ተመለስኩ፡፡

ሮዝ መጽሄት ሚያዚያ 2002 ዓ.ም.

## በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ሴቶች

- ✓ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዝዳንት....ፕሬዝዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ
- ✓ የኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሮፌሰር.....ፕሮፌሰር ዶክተር የአለምፀሃይ መኮንን
- ✓ የኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የፓርላማ ተመራጭ.....ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ
- ✓ ኢትዮጵያዊቷ/አፍሪካዊቷ የመጀመሪያዋ ፓይሌት....ወ/ሮ ሙሉመቤት እምሩ
- ✓ ኢትዮጵያዊቷ የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ ....ወ/ሮ ሮማን ወርቅ ካሣሁን
- ✓ ኢትዮጵያዊቷ የመጀመሪያዋ ነርስ /ሴት አስታማሚ.....ልዕልት ፀሐይ ኃ/ሥላሴ
- ✓ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት/አፍሪካዊት በኦሎምፒክ በማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ.....ሻለቃ ፋጡማ ሮባ
- ✓ ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ ጌምስ ሜዳሊያ ያስገኘች አትሌት .....ወ/ሮ ዘውዴ ሀ/ማርያም
- ✓ የመጀመሪያዋ በኢትዮጵያ ብስክሌትን የነዱ ሴት.....ወ/ሮ እቴጌ ጣይቱ
- ✓ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ቡና ቀማሽ.....ወ/ሮ የኔነሽ ደምሴ
- ✓ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት/አፍሪካዊት የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ.....ሻለቃ ደራርቱ ቱሉ
- ✓ የመጀመሪያዋ ፕሮፌሽናል ሴት ተዋናይት.....ወ/ሮ ሰለሞዊት ገብረሥላሴ

# የሴቶችን መማር አስፈላጊ የሚያደርጉ 10ሩ ምክንያቶች

በሎረን ስቴፕ

ከካይሮ እስከ ቤጂንግ በየትኛውም የዓለም አካባቢ ለወጣት ልጃገረዶች ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት መስጠት ለአንድ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ እድገት ዓይነተኛ አስተዋፅኦ አለው። ካርላ ኮፔል የተባሉ የየናይትድ ስቴትስ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) ሃላፊ የነበሩ ከዚህ ከፍ ባለደረጃ የሴቶችን ትምህርት አስፈላጊነት ይገልፁታል::እንደሃላፊው ገለፃ ከሆነ፣ ለሴቶች ትምህርት የሚሰጥ ትኩረት አድገትን በእውቀት ጎዳና ለመምራት ቀላልና ምትሃታዊ መፍትሄ (Silver bullet) ተደርጎ የሚቆጠር ነው። የጥቂት መጻህፍትና የአንድ መማሪያ ክፍል በተለያየ መልኩ በእድገትና በለውጥ እርምጃዎች ላይ የሚኖራቸውን አይነተኛ አስተዋፅኦ፣ የሴቶችን ትምህርት አስፈላጊ ከሚያደርጉ ከሚከተሉት 10 ምክንያቶች በዋናነት እንረዳለን።

የሴቶችን ትምህርት አስፈላጊነትን የሚያጎሉ 10 ምክንያቶች

መሠረታዊ ትምህርትን ማስፋፋት (Increased Literacy)፡- በዓለም አቀፍ ደረጃ መሠረታዊ ትምህርት አለገኘም ተብሎ ከሚገመተውና 163 ሚሊዮን ከሚጠጋውና በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ 63% የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። ሰለሆነም፣ ለሁሉም ልጆች ትምህርት ተደራሽ የሚሆንበትን ስልት ቀይሶ መንቀሳቀስ፣ መሃይምነትን በእጅጉ እንዲቀንስ ያደርጋል፤ የተማረውን ህዝብ ቁጥርንም ይጨምራል፡ ይህ ደግሞ በበኩሉ ለሃገራት ሁለንተናዊ እድገት አስተዋፅኦ ያደርጋል። በተለይም በማደግ ላይ ለሚገኙ ሃገራት የሚኖረው ጥቅም እጅግ አስፈላጊ ነው።

ህገወጥ የሰዎች ዝውውር መገደብ (Human Trafficking) ፡- እንደሚታወቀው ሴቶች ለሰዎች ዝውውር በይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸው ይታወቃል፡ ለዚህ ደግሞ በዋናነት ሰበብ ሆኖ የሚጠቀሰው አለመማራቸው ፣ በድህነት ውስጥ መኖራቸው መሆኑን/ እንደሆነ የሰዎችን ህገወጥ ዝውውርን በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተከላካይ ፕሮጀክት (United Nations Inter-Agency Project on Human Trafficking/UNIAP) ይጠቅሳል። እንደ ፕሮጀክቱ ከሆነ፣ ለወጣት ልጃገረዶች የተለያዩ እድሎችን ማመቻቸት መሰረታዊ የሆኑ ክህሎቶችን ማስጨበጥ ባለብዙ ቢሊዮን ዶላር ኢንደስትሪ እንደሆነ የሚቆጠረውን ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን በእጅጉ መቀነስ ይቻላል።

ፖለቲካዊ ውክልና (Political Representation)፡- በዓለም አቀፍ ደረጃ ሴቶች በምርጫ ሂደት ውስጥ ያለቸው ውክልናም ሆነ፣ በፖለቲካ ውስጥ ያለቸው ተሳትፎ በጣም የተገደበ ነው፤ በተፅእኖ ስርም የወደቀ ነው። በሴቶች አመራርና ተሳትፎ ዙሪያ የሚሰራው UNITED NATIONS WOMEN'S PROGRAMS ON LEADERSHIP AND PARTICIPATION እንደሚጠቅሰው፣ ለዚህ አንደኛው መፍትሄና በዚህ ረገድ የሚታየውን ክፍተት ለማጥበብ የሥነዜጋ ትምህርትና ስልጠና እና ሌሎች ሴቶችን ማብቃት ላይ አስተዋፅኦ ላላቸው ተግባራት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ነው።

ልጆችን በአንክብካቤ ማሳደግ (Thriving Babies) ፡- እንደተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሴቶች ትምህርት ኢኒሼቲቭ (UNITED NATIONS GIRLS' EDUCATION INITIVE/UNGEI) ከሆነ፣ ከተማሩ ሴቶች የተገኙ ልጅት ካልተማሩት ሴቶች ይልቅ ከአምሰት ዓመት በላይ የመቆየት እድላቸው በጣም ከፍተኛ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ ለትምህርት ቤት ግንባታና ለመማር ማስተማሩ አጋዥ ለሆኑ ካሪኩለም ነክ ጉዳዮች የሚደረግ ድጋፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው በምሥራቅ አፍሪካ በምትገኘውና በዓመት አስከ 16000 ልጆቿ በጨቅላ እድሜቸው የሚሞቱባትን ቡሩንዲን በከፍተኛ ደረጃ ጠቅሟል።

ከዖታዊ ግንኙነት መጠበቅ (Safe sex) ፡- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ሴቶች በሶስት እጥፍ ባነሰ ደረጃ ለኤችአይቪ የመጋለጥ እድላቸው ያነሰ ነው። ይህንን ስታትስቲካዊ መረጃ መሰረት ያደረገው የዓለም ባንክ፣ ትምህርት ልጆችን ከኤችአይቪ/ኤድስ ከመታደግ አንፃር ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን አረጋግጧል።

የጋብቻ መዘግየት (Later marriage) ፡- በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስነህዝብ ፈንድ (UNITED NATIONS POPULATION FUND) እንዳመለከተው፣ በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች ከሶስት ልጅገረዶች መካከል አንዷ 18 ዓመት ሳይሞላት ትዳር እንድትመሰርት ትደረጋለች። በአንፃሩ፣ ለሰባትና ከዚያ በላይ በትምህርት ዓለም የሚቆዩ ሴቶች ባሉባቸው ሃገሮች፣ የሴቶች በትዳር ዓለም ውስጥ የሚገቡበት ጊዜ በአራት ዓመት የሚዘገይ ሲሆን ይስተዋላል።

የቤተሰብ ብዛትን መመጠን (Smaller families) ፡- በትምህርት የመሳተፍ እድል በጨመረ ቁጥር የመውለድ ምጣኔን በጊዜ ሂደት እንዲቀንስ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ በማሊ የሁለተኛ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ትምህርት ያላቸው ሴቶች በአማካይ የሚኖራቸው የልጆች ብዛት በ3 ብቻ የተገደበ ነው። በአንፃሩ፣ በትምህርታቸው ያልገፉ ወይም የትምህርትን ደጃፍ ያልረገጡ ሴቶች በአማካይ ሰባት ልጆች ይኖራቸዋል።

የገቢ አቅም ማደግ (Income potential) ፡- ትምህርት ሴቶችን ከሚረዳቸው/ከሚያግዛቸው ነገሮች መካከል አንዱ ለገቢ አድገታቸው መጨመር ያለው አስተዋፅኦ ነው። የተማሩ ሴቶች የገንዘብ ቦርሳቸው ካልተማሩት ይልቅ በገንዘብ የመታጨቅ እድሉ ከፍተኛ ነው፡ ገንዘብ የሚያገኙበት እድል የሰፋላቸው ናቸው። እንደተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) ጥቆማ ከሆነ፣ የአንድ ዓመት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ብቻ ያገኘች ሴት፣ ይህ ትምህርት በራሱ በቀሪ ህይወቷ ላይ የምታገኘውን ገቢ በ20% እንደሚያሳድግለት መረጃዎችን ዋቢ በማድረግ ይጠቅሳል።

ለዓመታዊ ጠቅላላ የሃገር ውስጥ ምርት የሚኖር ድርሻ (Thriving GDP) ፡- ሴት ልጆችም ሆኑ ወንዶች ልጆች፣ ከዖታዊ አድልዎ በፀዳ መልኩ በትምህርት እንዲሳተፉ መደረጋቸው ለአንድ ሃገር ዓመታዊ ጠቅላላ ዓመታዊ ምርት መጨመር የራሱ ድርሻ አለው። 10% የሚሆኑ ሴቶች ትምህርት የሚያገኙበት እድል በጨመረ ቁጥር ደግሞ፣ የአንድ ሃገር ዓመታዊ ምርት በ3% ያድጋል።

ድህነት ቅነሳ (Poverty reduction) ፡- ሴቶችን ለትምህርት እድል እኩል መብትና ተደራሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ፣ በአንድ ሃገር የንግድና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖራቸውን የነቃ ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ይቻላል። ይህ ደግሞ፣ በሴቶች የገቢ ምንጭ መዳበር ላይ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ግልፅ ነው። ከዚህ በተጨማሪም፣ የሚያጋጥማቸውንም ሆነ ወደፊትም ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ድህነት መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን በማሟላት እንዲቋቋሙ አይነተኛ እድልም ይሰጣቸዋል። ያሉበትን ቤተሰብ ጭምር በማናቸውም መልኩ የመደገፍ ሚና እንዲኖራቸውም ያደርጋቸዋል።

በአጠቃላይ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሃገራት ቀጣይነትና እድገት በዋናነት ከሚመሰረትባቸው ጉዳዮች መካከል እንደቁልፍ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው የሴቶች ትምህርት ነው። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝደንት ባራክ አባማ ቀደም ብለው ጊዜ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ2012 አጠቃላይ ጉባኤ ላይ እንደተናገሩት "ቀጣዩ ጊዜ ሴቶችን በጉልበት ሊጫኑ ለሚሞክሩ ሁሉ ሊሆን አይገባም። ስለሆነም፣ ይህ ቀጣይ ጊዜ ሊቀረፅ የሚገባው፣ ትምህርት ቤት በሚሄዱ ልጃገረዶችና እንደወንዶች ልጆቻችን ሁሉ ሴት ልጆቻችንም ህልማቸውን አውን የሚደርጉባትን ዓለም እንድትኖር ጥረት በሚያደርጉ ሁሉ ነው::

## የማስተርካርድ ስኮላርሽፕ የ4ኛው ዙር የተጠቃሚ ተማሪዎች ምረቃ ሥነስርዓት

ቢሾፍቱ ባህርዳር

















# Message from FAWE Ethiopia Executive Director



As it is known that a feasible education policy has been formulated and implemented for several years in our country. Even though the policy has implemented with notable successes, it has also been accompanied with various challenges due to several economic and social problems pertaining in the country. Out of these challenges, problems that hinder the provision of quality and equitable education are the main ones that still need particular attention. To this effect, it is quite essential for all responsible and concerned bodies to give more attention by mobilizing their natural, human and financial resources and maximizing their efforts in order to alleviate the education sector's different challenges.

Various studies indicate that the number of females exceed the number of males in our country, Ethiopia. These studies also apparently state that our multifarious problems, especially the social and family responsibilities, are mostly shouldered on females in most parts. These challenges in turn affect negatively the active participation of females in the education sector and in programs that impacts the development and progress of the country. Thus, all concerned bodies are expected to mobilize their human and financial resources and maximize their concerted efforts in full for making visible changes in order to accomplish significant and considerable activities helpful to overcome the different educational problems of females in our country.

In order to meet the ever-growing demand of girls' educational access in our country, the role of non-governmental organizations (NGOs) is very pivotal and irreplaceable. In this respect, among these NGOs, which is vigorously engaged for ensuring the much needed enhancement of female education is FAWE Ethiopia. FAWE Ethiopia, having established as non-governmental organization in 1994, designed educational programs to assist female students who have been vulnerable to various economic and social problems. Since then, it has registered numerous fundamental contributions in making changes for girls' educational access.

FAWE Ethiopia, since its foundation, has progressively continued to extend its programs and has come to the rescue of girls who have been impeded from their schooling as a result of social and economic obstacles. The students who have been supported by its various programs have succeeded in their educational careers at secondary and tertiary levels of education and they are living witnesses of the great and fruitful interventions being made by FAWE Ethiopia.

Finally, I would avail of this opportunity to extend my cordial gratitude on behalf of the organization to the government and non-governmental organizations for their noble and lofty contributions in FAWE Ethiopia's programs which enabled various citizens who have become efficient and responsible bodies to meet the developmental needs of the country. Moreover, I hereby want to express my hope that FAWE Ethiopia, as it did before, would strengthen its ties with these organizations and proceed with its programs diligently and consciously on the basis of its objectives in order to extend its success story in the education sector.

# Overview of FAWE Ethiopia's Annual Accomplishments in the year 2021

FAWE Ethiopia Chapter is a member of Pan African organizations and one of the 34 FAWE Chapters in African Continent was established as local charitable organization in 1994 and re-registered as civil society organization in 2019. Since its inception, FAWE Ethiopia, with its collaborative local and foreign organizations, has been at the forefront of supporting girl students who have many challenges in accomplishing their education. Accordingly, thousands of these vulnerable students have benefited and got an opportunity to accomplish and continue their education at various levels with a success. Currently, FAWE Ethiopia is implementing five projects namely, the MasterCard Foundation Scholars Program, Break Free, Malala Foundation Global COVID-19 Initiative, Make Way and CSSP2 granted Bearers of Life at national level and in 4 regions (Amhara, Oromia, Sidama, and Addis Ababa).
FAWE Ethiopia, along with the continued impact of the Covid-19 pandemic, registered another successful achievement in 2021. Based on the annual plan approved for the year, summary of the main activities carried out, problems faced and solutions taken were presented under the major programs and projects of the organization.

## The MasterCard Foundation Scholarship Program

**The Program** provides academically talented, yet financially disadvantaged young people, particularly from Africa, with access to quality and relevant secondary and university education. Students selected for the Program receive a holistic set of financial, social and academic supports throughout their education and during their post-graduate transitions. The Program consists of a global network of education institutions and non-profit organizations, who together believe that education is a catalyst for social and economic betterment. Supported by MasterCard Foundation (MCF), this ten-year program was launched in August 2013 and is being implemented by Forum for African Women Educationalists (FAWE) through the respective National Chapters in Ethiopia and Rwanda and it runs until December 2023.
In **Ethiopia**, MCF Scholarship Program at FAWE Ethiopia offers a Comprehensive Scholarship package to 800 (600 girls and 200 boys) throughout secondary school (Grades 9 to 12). The Program aims at providing bright, yet disadvantaged students with the necessary scholastic material and empowerment support so as to acquire essential knowledge and skills through delivery of quality education. This will enable them to access better livelihoods and contribute to the household, community and national development. The Program is currently implemented in eight partner schools, both private and public, located in four marginalized localities where gender disparities in education are most notable: Bahirdar city in Amhara Regional State, Adama city in Oromia Regional State, Hawassa city in the Southern Nations and Nationalities People's Regional state (currently Sidama Regional State) and marginalized parts of Addis Ababa city administration. To achieve these goals of the program, different activities were planned and executed during 2021. Highlights of the main activities are as follows.

- Following the Regional level review and planning meetings held in Q1, FAWE Ethiopia hosted the National level annual review and planning meeting with the participation of 50 representatives of all key stakeholders drawn from regional and town level Finance and Economic Development, Women, Children and Youth and Education offices, Teacher Mentors, School Heads, selected scholars and FAWE Ethiopia staff. FAWE Ethiopia program, monitoring and evaluation team presented accomplishments of 2020, scholars' academic performances, research findings; factors affecting scholars' academic performance and a comparative analysis of academic performances of scholars vis-a-vis non-scholars of MasterCard scholars' program target schools.
- **2021 annual scholars' conference:** The 2021 annual conference was successfully organized for FAWE-MCF 5th cohort Scholars at JeCCDO training center, Bishoftu Town, from 4 to 5 August 2021. Eighty-nine (female 66 and male 23) 5th cohort scholars from Hawassa, Adama, and Addis Ababa attended the event where they were trained on Youth Adolescent Sexual Reproductive Health and Leadership Skills. Additionally, 2 (female 1 and male 1) alumni members attended the convening and presented their give-back activities in their communities. Fifth cohort scholars from Bahirdar were not able to attend the annual scholars' conference organized in Bishoftu town. Therefore, 2021 Annual Scholars' conference for Bahirdar scholars was held separately on September 16, 2021 at Tana-Haik Secondary School in Bahirdar City. Accordingly, 41 (female 27 and male 14) 5th cohort Bahirdar scholars attended the convening where they were also attended the training on Youth Leadership skills.
- Conducted graduation ceremony for the 3rd cohort scholars in the presence of representatives from Ministry of Education, principals of partner schools, government officials from line sector offices and FAWE Ethiopia board and staff. Overall Best performers of both sexes among FAWE Ethiopia scholars from were awarded with 6 laptop computers and regional high scorers have got 6 smart phones. Unfortunately, our scholars from *Bahir Dar* city could not participate in the graduation ceremony which was held at *Bishoftu/Debre Zeit* and hence organized a separate mini graduation ceremony at *Jakaranda* hotel, Bahir Dar city.



Reader Assisted Computer Literacy training participant visually impaired scholar

- Reader Assisted Computer Literacy training was provided for five visually impaired scholars at *Tana Haik* Secondary School, *Bahir Dar* City in collaboration with **Network of Organizations of/for the Visually Impaired and the Blind (**NOVIB) for 18 days (May 19-June 5, 2021) laptops were provided for the scholars in the presence of officials from Partner Schools and Regional Government Offices.
- **Training:** Training was conducted on *Psychological First Aid and Positive Discipline* by IMPACT Psychological and Health Services Consulting PLC to 18 (female 8 and male 10) teacher mentors and school counselors from partner schools and FAWE Ethiopia Career Guidance and Counseling (CGC) Officers at JeCCDO Training center, Bishoftu town, Ethiopia from 4 to 8 August 2021. Furthermore, *English language proficiency training* was conducted for 4th and 5th cohort scholars of Adama and Hawassa and 4th cohort scholars of Bahirdar. Albert Institute, Divine Sparks, $H_2O$ and Galaxy Language centers provided the training to Addis Ababa, Hawassa, Adama and Bahirdar scholars respectively; A total of 183 (female 120 and male 63) 4th and 5th cohort scholars have been provided with English language proficiency training. Moreover, *Entrepreneurships, Life Skills and ICT training* was provided to 4th and 5th cohort scholars in all project areas. Digital Opportunity Trust (DOT) Ethiopia provided/ conducted Entrepreneurships, Life Skills and ICT training to 5th cohort scholars in Adama and Hawassa, and 4th cohort scholars in Addis Ababa and Bahirdar for one month for each. A total of 181 (female 130 and male 51) Scholars attended Entrepreneurships, Life Skills and ICT training. At the end of these trainings, FAWE Ethiopia organized graduation programs for scholars who have attended the trainings in the respective project areas.



Psychological First Aid and Positive Discipline training

- The teacher mentors 4(2F) in Adama, 3(2F) in Hawassa, 3(2F) in Bahirdar, and 1(F) in Addis Ababa have been conducting individual mentorship with scholars, gave them guidance and advise about their studies, COVID-19 protection measures and other issues scholars need to talk about.




MasterCard Foundation scholarship program annual review meeting participants

- **Mid-term review meeting carried out**: The mid-term review meeting here referred to the mid-term of the second 5 years/second phase of MCF scholarship program. In view of that, FAWE Ethiopia Chapter in collaboration with key partners conducted mid-term review meeting of the second phase of MCF scholars program in Addis Ababa on 13 Aug, 2021, Adama 17 Aug, 2021, and Bahirdar 26 Aug, 2021. Key signatory government partners including Bureaus of Finance, Bureaus of Education, Addis Ababa (Kolfe-Keranio Sub-city) administration, Bahirdar City Administration, Adama City Administration and representatives of partner schools attended the mid-term review meetings in their respective project areas.

- **Tutorial programs** were commenced for most of the scholars. The session began with the pre-tutorial exams of that specific cohort (grade) in their respective schools to provide baseline comparative data for the post- tutorial assessment. In addition, strong follow up and support was being provided to the scholars to ensure 100% attendance and retention in the tutorial program. Consequently, almost all of the scholars were attending the tutorial. In this reporting period, 12(9F) vulnerable scholars were identified and supported with medical support from the COVID-19 response budget and from the insurance.
